# የግብረ ገብ ትምህርት
# የተማሪ መፅሐፍ

## 4ኛ ክፍል

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ
ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስተር

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ከተማ
አስተዳደር ትምህርት
ቢሮ

የግብረ ገብ ትምህርት የተማሪ መፅሐፍ አራተኛ ክፍል




የግብረ ገብ ትምህርት
የተማሪ መፅሐፍ

4ኛ ክፍል





የኢትዮጵያ ፌደራላዊ
ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስተር

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ከተማ
አስተዳደር ትምህርት
ቢሮ

# ይህ መጽሐፍ በጥንቃቄ ይያዝ!




ይህ የመማሪያ መጽሐፍ የትምህርት ቤታችሁ ንብረት ነው። ስለዚህም እንዳይጎዳ ወይም እንዳጠፋ አስፈላጊውን ጥንቃቄ አድርጉ። መጽሐፉን በጥንቃቄ ለመያዝ ይረዷችሁ ዘንድ የሚከተሉትን 10 ነጥቦች አስተውሉ።

1. መጽሐፉን እንደ ፕላስቲክ፣ ጋዜጣ እና በመሳሰሉ ቁሶች መሸፈን፣
2. መጽሐፉን ንጹህ እና ደረቅ ቦታ ማስቀመጥ፣
3. መጽሐፉን በሚጠቀሙ ጊዜ እጅዎት ንጹህ መሆኑን ማረጋገጥ፣
4. በመጽሐፉ ሽፋንም ሆነ የውስጥ ገጾች ላይ አለመጻፍ፣.
5. ገጾችን ከማጠፍ ይልቅ ቁራጭ ወረቀት ወይም ካርድ ለምልክት መጠቀም፣
6. ማናቸውንም ምስሎች ወይም ገጾችን ፈጽሞ አለመቅደድ፣
7. ማናቸውንም የተቀደዱ ገጾች መጠገን፣
8. መጽሐፉን በቦርሳ ውስጥ በጥንቃቄ ማስቀመጥመጽሐፉን
9. ለሌላ ሰው ሲያውሱ በጥንቃቄ ማቀበል፣
10. አዲስ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲጠቀሙ፤ መጽበጀርባ ሽፋኑ በኩል ማስቀመጥ ከዚያም በአንድ ጊዜ ውስን ገጾችን መግለጽ፤እንዲሁም የመጽሐፉን ጠርዞች በትንሹ ጫን ጫን ማድረግ። ይህም የመጽሐፉ ሽፋን በጥሩ ሁኔታ እንዲቆይ ይረዳል።



# የግብረ ገብ ትምህርት
# የአራተኛ ክፍል
# የተማሪው መጽሐፍ


አዘጋጆች ቂጤ በዳሳ ጩፊቄ (M.A)

መሀመድ ደመር አርጋዉ (M.A)

አርታዒዎች ዳኘ ጥላሁን አሰፋ (M.A)

ጀንበ ጉዱፊ ፈጋ (M.A)

ዶ/ር አባቡ ተፈራ አዱኛ (P.H.D)

ሰዓሊ ዋሲሁን ዳኘ ምህረቴ (M.Sc)

ሌይአዉት ዲዛይነር አብርሃም ሰሎሞን (B.Sc) (አስማምቶ የሰራዉ)

ዳዊት ደጀኔ ቢቂላ (M.Sc)

ተርጓሚዎች ዋሲሁን በድሉ (M.A)

ጋሪደዉ ነገራ (M.A)

አርታኢና ገምጋሚ በላይ በለጠ (M.A)

አስተባባሪ ጊታቸዉ ታስማ (M.A)



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስተር

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

## ምስጋና

ይህ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ትምህርት ሚኒስቴር፤ በአለም ባንክ እንግሊዝ አለማቀፋዊ ልማት ድጋፍ በፊንላንድ የውጭ ጉዳይ፤ በኖርዌይ ኢምባሲ፤ ዩኒሴፍ፤ በአለም አቀፍ የትምህርት ጥምረት፤ በዴንማርክ የውጭ ጉዳይ ሚንስቴር እና በመልቲ ዶነር ትረስት ፈንድ በ2015 ዓ.ም ታተመ፡፡

©2015 በኢትዮጵያ ዴሞክሲያዊ ሪፐብሊክ፤ ትምህርት ሚኒስቴር የህትመት መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ይህን መጽሐፍ በግል ደረጃ ማባዛት፤ መተርጎም ወይም በቅጅ ለሌላ ጥቅም ማዋል በሕግ የተከለከለ ነው፡፡

የትምህርት ሚኒስቴር በዚህ መጽሐፍ ህትመት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አስተዋፅኦ ያደረጉትን ግለሰቦች እና የመንግስት አካላት ከልብ ማመስገን ይፈልጋል፡፡ በመቀጠለም በሐዋሳ፤ በአዲስ አበባ እና በጅማ ዩኒቨርስቲዎች ይህ መጽሐፍ ለዚህ እንዲበቃ ያደረጉትን ጉልህ አስተዋፅኦ የላቀ ምስጋና ይድረሳቸው፡፡

ይህን መጽሐፍ ያለ ባለቤቱ ፍቃድ ወይንም እውቅና አባዝቶ ሲጠቀም
የተገኘ ሰው /ተቋም ካለ ወደ ዋና መስርያ ቤቱ በመምጣት ወይም በፖ/
ሳ/ቁ. 1367 አ.አ ይጠቁሙን፡፡

የታተመው---------------------------------------

---------------------------ሕትመት ድርጅት

ፖ/ሳ/ቁ. ----------------------------------------

---------------------------------------ኢትዮጵያ

በትምህርት ሚኒስተር የውል ስምምነት ቁጥር

# ማውጫ

ይዘቶች ገፅ


ምዕራፍ አንድ ........................................................................................1

ለራስ የሚሰጥን ዋጋ/ግምት መገንባት...........................................................1

1.1 ለራስ የሚሰጥ ዋጋ ወይም ግምት.....................................2

1.2 ለራስ የሚሰጥ ግምት ወይም ዋጋ መገለጫዎች....................4

1.2.1 ራስን መቻል.......................................................5

1.2.2 በራስ መተማመን..................................................6

1.2.3 ራስን መቆጣጠር..................................................9

1.3 ለራስ የሚሰጥን ግምት ለማሻሻል የሚረዱ መንገዶች................10

1.4 ለራስ የሚሰጥ መልካም ግምት ጠቀሜታዎች.......................11

1.5 ችግርን የመቋቋም/የመጋፈጥ/ ብቃት....................................11

1.6 ለራስ የሚሰጥ ዋጋ ማነስ ያለው አሉታዊ ተጽዕኖ .................12

የምዕራፉ ማጠቃለያ.........................................................................14

የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች ..............................................................15

ምዕራፍ ሁለት........................................................................................17

ሰብዓዊ መብቶችን መረዳት/መገንዘብ........................................................17

2.1 የስብዓዊ መብቶች ምንነት ...............................................18

2.2 ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር ጠቀሜታ ..............................19

2.3 ሰብዓዊ መብቶችና ኃላፊነት...............................................20

2.4 የሰውን ክብር ማክበር.........................................................23

2.5 የሕፃናትን መብት ማክበር...................................................24

2.6 የሴቶችን መብት ማክበር ...................................................26

2.7 የአካል ጉዳተኞችን መብት ማክበር......................................27

የምዕራፉ ማጠቃለያ.....29
የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች.....30
ምዕራፍ ሦስት .....32
ሰላም.....32
3.1 ሰላም.....33
3.2 የሰላም ጠቀሜታ.....36
3.3 ሰላምን ለማሻሻል ሚረዱ መንገዶች.....36
3.4 ግጭትን በሰላም መፍታት.....40
3.5 የሰላም ዕጦትና ውጤቱ.....43
የምዕራፉ ማጠቃለያ.....45
የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች .....46
ምዕራፍ አራት.....48
በማህበራዊ ክዋኔዎች ጊዜ መታየት ያለበት ስነ- ምግባር .....48
4.1 የስነ ምግባር ትርጉም.....49
4.2 በማህበበራዊ ክዋኔዎች ጊዜ የሥነ-ምግባር አስፈላጊነት.....52
4.3 የዕረፍት ጊዜን በአግባቡ መጠቀም.....54
4.4 በማህበራዊ ክዋኔዎች ውስጥ የሚደረጉ እና የማይደረጉ ጉዳዮች...56
4.4.1 የመንገድ እንቅስቃሴና ደህንነት .....64
4.5 በማህበራዊ ግልጋሎት ውሰጥ የሥነ-ምግባር መርሆዎች..... 67
የምዕራፉ ማጠቃለያ.....69
የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች .....70

ምዕራፍ አምስት ....................................................................73

የመቻቻል ባህል ....................................................................73

5.1 የመቻቻል ባህል ፅንሰ ሐሳብ..........................................................74

5.2 የመቻቻል ባህል ይዘቶች ..........................................................75

5.3 የመቻቻል ባህል ጠቀሜታ..........................................................76

5.4 በመቻቻል ባህል ላይ ተፅዕኖ የሚያመጡ /የሚያሳድሩ ጉዳዮች.....77

የምዕራፉ ማጠቃለያ....................................................................79

የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች ..........................................................80

ምዕራፍ ስድስት....................................................................82

የባህል ብዝሀነት ማቻቻል ..........................................................82

6.1 የባህል ብዝሀነት እና መቻቻል ..................................................83

6.2 በብዝሃነት ውስጥ የአንድነት አስፈላጊነት..................................86

6.3 በባህል ብዝሃነት ውስጥ የመቻቻል ጠቀሜታ............................90

6.4 ብዝሃ-ባህልን ማስተናገድ..........................................................92

የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች ..........................................................95

የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች ..........................................................96

# መግቢያ

ሰዎች ማህበራዊ እና ምክንያታዊ እንስሳት ናቸው፡፡ የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጥረታት የሚለዩት ልዩ ባህሪያት አሉት፡፡ልዩ የሆነ ባህሪ ያለዉ የሰው ልጅ ብቻ ነው፡፡ ባህሪ ማለት በሰዎች የሚገነባ ሆኖ ትክክል እስከሆነ ድረስ ሰዎች ያቀዱትን ግቦች ለማሳካት የሚየስችላቸዉ ነዉ፡፡ባህሪን ለመገንባተ የሰው ልጅ በምክንያታዊነት እና በግብረገብ መርሆዎች ላይ የተመሰረተ የድርጊት መርሃ ግብሮች ያስፈልጋቸዋል፡፡ ባህሪ ሌሎችን በመምሰል የሚመሰረት አይደለም፡፡ ምክኒያቱም ባህሪ ግለሰባዊ በመሆኑ እና የሚመራው በግለሰቡ አስተሳሰብ በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም የሰው ልጅ በምድር ላይ ካሉ ፍጥረታት የሚለየዉ በምክኒያት እና በህሊናዊ እዉነታ መመራቱ ነው፡፡እዉነታዉም የሚያሳየዉ የሰዉ ልጅ የግብረ ገብ ግዴታዉን ለመፈጸም የሚያስችሉት ብቃት እና ችሎታ ያለዉ ስለመሆኑ ነዉ፡፡

ግብረ-ገብነት የብዙ መመሪያዎች ስብስብ ነዉ፡፡ የሰው ልጅ ምንም እንኳን በእነኝህ መመሪያዎች የተወሰነ ነጻነቱ ቢገደብም ለእነኝህ መመሪያዎች እራሱን ማስገዛት እንዳለበት ይታመናል፡፡ ይህንን እዉነታ መሰረት በማድረግም የሰዉ ልጅ በዚህ ዉስብስብ በሆነ ዓለም አብሮነታቸዉን ያዳብራሉ፡፡ ደህንነታቸዉን ያስጠብቀሉ፡፡ እንዲሁም ነጻነታቸዉን ያስከብራሉ፡፡ ሰፋ አድርገን ስናየዉም ግብረገብነት የሚከተሉት አላማዎች አሉት፡፡ 1ኛ፡ ማህበረሰብን ከውድቀት ወይም ከብተና ማትረፍ፡፡ 2ኛ፡ የሰው ልጅ መከራን መቀነስ፡፡ 3ኛ፡የሰው ልጅ እድገትን ማጎልበት፡፡ 4ኛ፡ ግጭትን ፍትሃዊ እና ስርዓቱን በጠበቀ መንገድ መፍታት፡፡ 5ኛ ሽልማት እና ቅጣትን፡ ትችትን እና ሙገሳን በአግባቡ ለመስጠት፡፡ ግብረ-ገብነት የጋራ አላማን ለማሳካት አስቀድሞ የተቀመጠ የማህበረሰቡ ልማዳዊ ስርዓቶች ወይም መመሪያዎች ስብስብ ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ ለሰው ልጆች መኖር እና ማደግ የግብረ ገብ ትምህርት አስፈላጊ ነዉ፡፡ ነጻነቱን ያረጋገጠ ስልጡን ህዝብ ለመሆን ከቀድሞ በበለጠ የግብረ ገብ እሴቶቻችንን ማወቅ እና መኖር ይጠበቅብናል፡፡ ግብረ-ገብነት የተሸለ ህይወጽን ለመኖር የሚያስችለን ማህበረሰባዊ እሴት ነዉ፡ ፡ የትኛዉም ማህበረሰብ የራሱ የሆነ የግብረ-ገብ ደንቦችና እሴቶች አሉት፡፡ ነገር ግን ሰዎች ለእነኝህ ግብረገባዊ ደንቦች እና መርህዎች እራሳቸውን እስካላስገዙ ድረስ የእነርሱ መኖር ብቻዉን ለሰዉ ልጆች ደህንነት መጠበቅ ዋስትና አይሆኑም፡፡ በመሆኑም እኛ እንደሰዉ እነኝህን የግብረ ገብ ደንቦች እና መርሆዎች ስንኖራቸዉ በሰዉ ልጆች ላይ የሚደርሱ ኢሰባአዊ ድርጊቶች፤ መከራ እንዲሁም ክፋት መቀነስ ብሎም መጥፋት ይጀምራሉ፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ የግብረ ገብ ትምህርት አዲስ ክስተት አይደለም፡፡ የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ትምህርቱ ለመጀመሪያ ግዜ መሰጠት የተጀመረው በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን እንደነበረ ነው፡፡ ነገር ግን ትምህርቱ ለንጉሱ እና ለመንግስታቸው ወገንተኝነት እንደነበረው ይታመናል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ አዲሱ ስርዓተ ትምህርት የተቀረጸው ተማሪዎቹ የባህሪ እና የአመለካከት ለዉጥ እንዲያመጡ ታሳቢ በማድረግ ነዉ፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ኃላፊነት የሚሰማዉ ዜጋም ለመፍጠር ነዉ፡፡ ትምርቱ በሚዘጋጅበት ጊዜም በተቻለ መጠን ኢትጵያዊ ይዘት እንዲኖረው ጥረት ተደረጓል፡፡ ትምህርቱ የተዘጋጀው በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት እንደመሆኑ ከ1ኛ-6ኛ ክፍል የተለየ ትኩረት በመስጠት ነው፡፡ በተለይ የ4ኛ ክፍል የግብረ ገብ ትምህርት የተለያዩ የግብረገብ እሴቶች ይዘትን ያካተተ ነው፡፡

ለአብነትም ለራስ ዋጋ መስጠት፤ሰብዓዊ መብቶችን ማክበር ፤ግብረገብዊ ሃላፊነቶችን መወጣት፤ የህጻናት ስነ ምግባር፤መቻቻል፤መልካም ጠባይ፤ ሰላም፤አብሮነት፤ሌሎችን ማክበር እና ብዙሃነት ናቸዉ፡፡ በአጠቃላይ የአዲሱ ስርዓተ ትምህርት የግብረገብ ትምህርት የተቀረጸዉ ተማሪዎቹ ክህሎትን፤እዉቀትን፤ ዝንባሌያቸውን ከፍ በማድረግ የማህበረሰቡን እሴቶች እንዲያዉቁ ና እንዲጠብቁ ለማስቻል ነው፡፡

ትምህርቱን በማስተማር በኩል ከሁሉም ነገር በላይ የመምህሩ ሚና ከፍተኛ ነዉ፡፡ መምህሩ ትምህርቱን በሚያስተምርበት ወቅት ማራኪ ለማድረግ አሳታፊ የማስተማር ዘዴን መጠቀም አለበት፡፡ የቀረቡትም ተግባሮች ለዚሁ አላማ የሚረዱ ናቸዉ፡፡ ዋናዉ ጉዳይ ተማሪዎቹ በተቀመጠዉ መመሪያ መሰረት ትምህርቱን ከተከታተሉ፤ ተግባራዊ ካደረጉ እንዲሁም የራሳቸዉን ፈጠራ ካከሉበት ለዚህ የክፍል ደረጃ የተቀመጠዉን ግብ ሊያሟኩ ይችላሉ፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## ለራስ የሚሰጥ ግምት/ዋጋን መገንባት

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፡-**

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ለራስ የሚሰጥ ግምት/ዋጋ ትርጓሜን ትገልጻላችሁ፡፡
- ለራስ ግምት መስጠት ያለዉን ጠቀሜታ ዋጋ ትሰጣላችሁ፡፡
- ለራሳችሁ ግምት እንድትሰጡ የሚረዷችሁን ስነ-ዘዴዎች ትገልጻላችሁ፡፡
- የእርግጠኝነት ባህሪያትን ታብራራላችሁ፡፡
- ተግዳሮቶችን ለመጋፈጥ የሚያስችሉ ክህሎቶችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ለራስ ዝቅተኛ ግምት መስጠት የሚያስከትለውን ችግር ትለያላችሁ፡፡

### መግቢያ

ባለፉት ክፍሎች እራስን  እና ሌሎችን ለመረዳት መሰረት ስለሆኑት ስለ ራስ መግዛት እና ስለ ራስ ክብር ጽንሰ ሃሳብ ተምራችኋል፡፡ ራስን ማክበር እና እራስን መግዛት  ደግሞ  እናንተ በራሳችሁ መተማመን፤ ስለ እራሳችሁ አዎንታዊ አስተሳሰብ እንዲኖራችሁ  ያስችላችኋል፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ ስለ እራስ ግምት መገንባት እና ስለ ማሻሻያ መንገዶች ትማራላችሁ፡፡

## 1.1 ለራስ ግምት/ዋጋ መስጠት

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

- ለራስ ከፍ ያለ ግምት መስጠት ማለት ምን ማለት ነው?
- ለራስ ከፍ ያለ ግምት መስጠት ምንጩ ምንድን ነዉ?

### መግቢያ

አንድ ሰው ለራሱ የሚሰጠው ግምት ወይም ዋጋ እና ያለው አረዳድ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን ይችላል:: አዎንታዊ የራስ ግምት የሚታየው እናንተ ለራሳችሁ ከፍተኛ ግምት ስትሰጡ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ አሉታዊ የራስ ክብር የሚታየው እናንተ ለራሳችህ ዝቅተኛ ግምት ስትሰጡ ይሆናል፡፡ እናንተ ለራሳችሁ አዎንታዊ የራስ ግምት ካላችሁ በራሳችሁ ችሎታና አቅም ትተማመናላችሁ፤ ጉዳዮችን በራሳችሁ አቅም ትሰራላችሁ፤ የተሻለ ስራ ለመስራትም ትነሳሳላችሁ፤ እንዲሁም በሰራችሁት ስራም ክብር ይሰማችኋል፡፡ በዚህም ምክንያት ለራስ ግምት መስጠት ማለት አንድ ሰው ለራሱ ያለው አመለካከት ወይም ባለው ችሎታ ያለው እምነት፤ በራስ አቅም በመተማመን ተግባሮችን መፈጸም መቻል ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ የቤት ስራ መስራት፤ ጠንክሮ ማጥናት፤ የፈተና ጥያቄዎችን በራስ አቅም መስራት፤ እንዲሁም ሌሎች የሚሰጡ ተግባራትን ማከናወንን ያካትታል፡፡

**ውስን ጥናት** - በፈተና ግዜ ተማሪው ለራሱ የሚሰጠው ግምት :
ከበደ የ4ኛ ክፍል ተማሪ ነው:: ብዙ ጊዜውን የሚያሳልፈዉ መጽሐፍ በማንበብ እና አልፎ አልፎም የእግር ኳስ ጨዋታዎችን በማየት ነው፡፡ የሚያነብበትን እና የሚጫወትበትን የጊዜ ዕቅድም አዘጋጅቷል፡፡ የትምርት ክፍለ ጊዜዉን በንቃት ይከታተላል ሁሉንም የሚሰጡ የቤት ስራዎቹን በአግባቡ ጠንክሮ የሚሰራ ተማሪ ነው፡፡ የትኛዉንም ኃላፊነት በራሱ ችሎታ እና አቅም መስራት እንዳለበትም ያምናል፡፡

ስለሆነም የክፍል ጓደኞቹን የሚሰጣቸውን የቤት ስራ እና ኃላፊነት በራሳቸው ችሎታ እና አቅም መስራት እንዳለባቸዉ ይመክራቸዋል፡፡ ኩረጃን ይጠየፋል፡፡ ፈተና ከመድረሱ በፊት ጠንክሮ ያጠናል፤ በፈተና ጊዜም ፈተናዉን ተረጋግቶ ይሰራል፤ ከፍተኛ ውጤትም ያስመዘግባል፡፡ በዚህም ምክንያት ከበደ ደስተኛ እና መንፈሰ ጠንካራ ሊሆን ችሏል፡፡ ከበደ ስለ እራሱ ሲናገርም እኔ ስኬታማ የሆንኩት ጠንክሬ ስለማጠና ነዉ ይላል፡፡

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

ለራስ ግምት /ዋጋ መስጠት ምነድን ነዉ?

ለራስ ግምት መስጠት ምንጩ ከየት ነው?



ስዕል. 1.1: ጠንክሮ የሚሰራ ተማሪ

- ለምን ከበደ በፈተና ጊዜ ደስተኛ እና የተረጋጋ ሊሆን ቻለ?
- ከፈተና በፊት ከበደ እራሱን እንዴት ነዉ የሚያስበዉ/የሚረዳዉ?

**ለራስ የሚሰጥ ዋጋ:** ለራስ የሚሰጥ ዋጋ ምን ማለት ነዉ?

ለራስ የሚሰጥ ዋጋ ማለት እኛ እራሳችንን የምናስበው እና እራሳችንን የምናይበት መንገድ ማለት ነው፡፡

**የጽብረቃ ተግባር 1.1**

1. እራሳችሁን እንዴት ታያላችሁ?
2. አስተዋይ ነኝ ብላችሁ ታስባላችሁ?
3. በቤተሰብ እና በክፍል ውስጥ ተፈላጊ ነን ብላችሁ ታስባላችሁ?

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

*ለራስ የሚሰጥ ዋጋ መገለጫ ባህሪያት ምን ምን ናቸዉ?

## 1.2 ለራስ የሚሰጥ ዋጋ መገለጫዎች

ለእራስ ግምት መስጠት የተለያዩ መሰረታዊ ባህሪያት አሉት፡፡ ዋና ዋናዎቹ ግን እራስን መግዛት፤ በራስ መተማመን እና ጥገኛ አለመሆን ናቸዉ፡፡ የሚከተለዉን ስለ አሚና እና ማቲዎስ የተጻፈዉን ተረክ አንብባችሁ ተከታዩን ጥያቄ መልሱ፡-

አሚና እና ማቲዎስ የትምህርት ቤት ጓደኞሞች ናቸው፡፡ እነሱ የተለያዩ ልምድና አቅም አጎልብተዋል፡፡ አሚና በማህበረሰባዊ እንቅስቃሴዎች ጥሩ ተሞክሮ ስላላት ቤተሰቦቿን፤ ጓደኞቿን እና የትምህርት ቤቷን ጨምሮ ከተለያዩ ሰዎች ጋር ትገናኛለች፡፡ ራሷን የምትገልጸውም ከእነዚህ አካላት ጋር ካላት ግኑኝነት እና ካካበተችው ልምድ አንጻር ነዉ፡፡ እንዲያም ሆኖ ግን እሷ በሌሎች መጥፎ ባህሪ ጫና ውስጥ ሳትወድቅ የምታደርጋቸዉ እንቅስቃሴዎች ጠቀሜታ እንዳላቸው ይታመናል፡፡

በተመሳሳይ ማቲዎስ በጥንካሬ የተገነባ ብቃት አለው፡፡ ከስኬት እና ከውድቀት የሚገኙ አዳዲስ ነገሮችን ይማራል ተሞክሮም ይወስዳል፡፡ በራሱ አቅም በመተማመንም የሚገጥሙትን ፈተናዎች ይጋፈጣል፤ ያቀደውን አላማም ያሳካል፡፡ ትምህርታዊ ኃላፊነቱን በራሱ ይፈጽማል፡፡

የእሱ ስኬት መሰረቱ በራስ የመተማመን ስሜት መኖሩ፤ ለራሱ የሚሰጠውን ግምት ማጎልበቱ እና አዳዲስ ተግዳሮቶችን መጋፈጡ ናቸዉ፡፡

### 1.2.1. ራስን መቻል

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

- ራስን መቻል ማለት ምን ማለት ነዉ?
- ጥገኝነት ምንድን ነዉ?

ጥገኛ አለመሆን ማለት በሌሎች ሰዎች ላይ ጥገኛ ሳትሆኑ በራሳችሁ አቅም ተግባራትን ማስተዳደርና ማከናወን መቻል ማለት ነው፡፡ጥገኛ አለመሆን የሚመነጨው የራስን ችግር በራስ አቅም መፍታት እችላለሁ ብሎ ከማመን ነዉ፡፡

**ሁኔታ 1፡** ጫልቱ ታታሪ የ4ኛ ክፍል ተማሪ ነች፡፡ የቤት ስራዋን በሰዓቱ ትሰራለች፡፡ እያንዳንዱን ትምህርት ለመረዳት የምትችለውን ሁሉ ትጥራለች፡፡ ብዙ ጊዜዋንም በማንበብ ታሳልፋለች፡፡ እውቀቷን ለማስፋት መጻሕፍትን ታነባለች፡፡እገዛ ሲያስፈልጋትም አስተማሪዎቿን እና የክፍል ጓደኞቿን እርዳታ ትጠይቃለች፡፡ ጫልቱ ሌላ ልዩ ችሎታም አላት ጠንክራ ትሰራለች፤ ፈተና ስትፈተንም በራሷ ትተማመናለች፤ የፈተና ክፍል ውስጥም የተረጋጋ፣ ዘና ያለ እና በራስ የመተማመን ስሜት ይኖራታል፤ ለፈተናዋም ትኩረት ትሰጣለች፤ ሁሉንም ጥያቄዎች ትሞክራለች እንዲሁም ፈተናውን በሰዓቱ ታጠናቅቃለች፡፡



ስዕል 1.2 ታታሪ ተማሪ በክፍል ዉስጥ ሲሳተፍ

ፅብረቃዊ ተግባር 1.3

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::

1. ጫልቱ በችሎታዋ ላይ የምትተማመን ይመስላችኋል?
2. እራሱን የቻለ ሰው ከጥገኝነት ነጻ የሆነ ይመስላችኋል?
3. ጫልቱ በጥናት ጊዜ ችግሮች ሲያጋጥሟት ሌሎችን እርዳታ ትጠይቃለች:: ይህ የጥገኝነት ምልክት ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?
4. ጥገኛ ያለመሆን ጥቅሞችን ቢያንስ ሁለቱን ጥቀሱ::

## 1.2.2. በራስ መተማመን

የማነቃቂያ ጥያቄ

- ለናንተ በራስ መተማመን ምንድን ነው?

በራስ መተማመን ማለት የሆነን ጉዳይ በራስ ብቃት ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማከናወን እርግጠኛ መሆን ነው::ይሄ ደግሞ የሚሆነው ራስን በትክክል ከመረዳት ነው:: በራስ መተማመን ሰዎችን በማነቃቃት በስራቸው ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ያደርጋቸዋል::

በራሱ የሚተማመን ተማሪ ትምህርቱን በትኩረት መከታተል፤ የቤት ስራዎችን እና ሌሎች የሚሰጡ ተግባራትን መስራት እንዲሁም በእቅዱ መሰረት ትምህርቱን ማጥናት ይችላል። በራስ መተማመን ለጠንካራ ስራ መሰረት ነው። አዎንታዊ አስተያየት እና ድጋፍ ተማሪው በራስ የመተማመን ስሜቱን እንዲያዳብር ሊረዱት ይችላሉ።

በራሱ የሚተማመን ሰው ለአዳዲስ ተግዳሮት ራሱን ያዘጋጃል፤ መልካም እድሎችን ይጠቀማል፣ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ያስተናግዳል እንዲሁም ችግሮች ሲደርሱም ሀላፊነትን ይወስዳል።

“በራስ መተማመን ሁል ጊዜ ትክክል ከመሆን ብቻ ሳይሆን መሳሳትን ካለፍርሃት በመቀበል የሚመጣ ነው።”

ይሄንን አባባል እንዴት ነው የተረዳችሁት?

**ዉስን ጥናት - ጽጌ እና ወንድሟ**

ጽጌ የ4ኛ ክፍል ተማሪ ነበረች። በትምህርቷ ጠንካራ ተማሪ አልነበረችም ስለሆነም በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ዝቅተኛ ውጤት አስመዝግባለች። ወንድሟ ደጉ በውጤቷ ይበሳጭ ነበር። እሱ ሁል ጊዜ ይመክራት የነበረዉ በደንብ እድታጠና እና በትምህርቷ ስኬታማ እንድትሆን ነበር። ወላጆቿ ፅጌን ከቤት ውስጥ ስራ ነፃ እንድትሆን በማድረግ ለትምህርቷ የሚያስፈልጉ ቁሶችን አሟልተዉላት ነበር። ከዚህ በተጨማሪም ጠንክራ እንድታጠና ያበረታቷት ነበር። ስለዚህም ጽጌ ሁሉንም ትምህርቶች ለመከታተል እና የቤት ስራዋንም በሰዓቱ ለመስራት የምትችለውን ሁሉ ለማድረግ ወሰነች። ከዚያም ጊዜዋን በአግባቡ በመጠቀም ለትምህርቷ የተለያዩ የማጣቀሻ መጽሃፎችን ማንበብ ጀመረች። የሚከብዳትንም ወንድሟን፣ አስተማሪዎቿን እና የክፍል ጓደኞቿን በመጠየቅ ለመረዳት ሞከረች ቀስ በቀስም የመማር ችሎታዋን በማሻሻል ጥሩ ውጤት ለማምጣት በቅታለች።

ወንድሟ ደጉ ጽጌን “አ! አንች እኮ በራስሽ አቅም ስኬታማ መሆን አትችይም ሁል ጊዜ የእኔን እርዳታ ትፈልጊያለሽ ሲላት እሷም አይደለም አንተ ልትመክረኝ ስትሞክር እኔ እያዳመጥኩህ ነበር፡፡
አሁን ግን አስደናቂ ለውጥ አሳይቻለው በእራሴ ነገሮችን ማስተካከል እችላለሁ፡፡ ብላ ትመልስለታለች፡፡ ይህ የሚያሳየው ፅጌ በእራሷ አቅም ውጤታማ መሆን እንደምትችል ነው፡፡ አክላም ወንድሜ “የመጨረሻው የፈተና ውጤቴ ላሳይህ ከበፊቱ የበለጠ ነው”፡፡ ወንድሟም ውጤቷን አይቶ በዛዉ እንድትቀጥል ነገራት፡፡



ስዕል 1.3 ወንድም እህቱን ሲመክር፡፡

ጽጌ በትምህርቷ በራስ መተማመንን እንዴት ልታሻሽል ቻለች?

1.4 የጽብረቃ ተግባር

1. የሚከተሉት ባህሪያት ዝቅተኛ የራስ መተማመን ያላቸዉ ተማሪዎች ውጤት እንደሆነ እና እንዳልሆነ ተወያዩ፡-

ሀ. አይን አፋርነት ለ. የተግባቦት ችግር ሐ. ስሜታዊነት

2. በራሳችሁ እንተማመናለን ብላችሁ ታምናላችሁ? ከሆነስ እንዴት?

3. ትምርትን ለማሻሻል በራስ መተማመን ምን ይጠቅማል?

4. በራስ መተማመናችሁን ለማሳደግ ምን ማድረግ አለባችሁ?

### 1.2.3. ራስን መግዛት

በሚከተለዉ ምሳሌያዊ አነጋገር ላይ አስተያየት ስጡ:

የራሳቸዉን ስሜት መግታት የማይችሉ ሰዎች የጠላት መከላከያ ግንብ እንደሌለው ከተማ ይመሰላሉ፡፡

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

ከላይ የተጠቀሰው ምሳሌያዊ አነጋገር ምን ማለት ነው?

በዚህ ትስማማላችሁ?

“ከተማን ከጠላት ከሚከላከል ግንብ እራሱን የሚገታ ሰዉ ይበልጣል፡፡”

እራስን መግታት የሚሳካዉ እኛ እራሳችንን ወይም ሌሎች ሰዎችን ሊጎዱ ከሚችሉ ድርጊቶችን ማድረግ ስናቆም ነዉ፡፡ ለምሳሌ፡- ከሌሎች ጋር በምንጫወት ጊዜ የእነሱን ክብር ላለመድፈር እና ላለማጣጣል ራሳችንን መግታት ይኖርብናል፡፡ አንዳንድ ሰዎች እራሳቸዉን መግታት ባለመቻላቸዉ የተነሳ በሚሰሩት ስራ እራሳቸዉን እና ሌሎች ሰዎችን ሲጎዱ ይስተዋላሉ፡፡ ስለዚህ እናንተን ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮችን ከማድረግ ተቆጠቡ፡፡

**የሚከተለዉን ሀተታ አንብቡ**

አንድ ቀን የተወሰኑ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ዉጪ እያወሩ ነበር፡፡ ሌላ ሰዉም መጣ እና ተቀላቀላቸዉ፡፡ ከዛም  ይሄው ግለሰብ ያለ ወላጆቻቸው ፍቃድ የሆነ ቦታ አብረዉ ሄደው የእግር ኳስ ጨዋታ ማየት ይፈልጉ እንደሆነ ጠየቃቸው፡፡ እነሱም ግለሰቡ ያቀረበላቸውን ጥያቄ በመቃወም አብረዉት ሳይሄዱ ቀሩ፡፡ ከትምህርት ቤት ሲመለሱም ወደ ቤታቸው በመሄድ ወላጆቻቸውን ያግዛሉ፡፡ ከቆይታ በኋላም ይሄው ግለሰብ ለብዙ ጊዜ ሲሰራው በነበረው ህጻናትን በማዘዋወር ወንጀል ተከሶ በፖሊስ ታሰረ፡፡



ፅብረቃዊ ጥያቄዎች1.5:

1. ከዚህ ሀተታ/አጭር ታሪክ ምን ተማራችሁ?
2. ከሌሎች የሚመጡ የአቻ ግፊቶችን ለመቋቋ ምን ማድረግ አለባችሁ?

## 1.3. ለራስ የሚሰጥ ግምትን /ዋጋን ማጎልበቻ መንገዶች

የማነቃቂያ ጥያቄ

*ለራስ የሚሰጥ ግምት/ዋጋን ማጎልበቻ ዘዴዎችን ዘርዝሩ፡፡

ለራስ የሚሰጥ ግምት/ዋጋን ለማጎልበት የሚረዱ ዘዴዎች አሉ፡፡

ለምሳሌ፡-

- የራስን ተሰጥኦ ማድነቅ እና እውቅና መስጠት፡፡
- አቋምን ማስተካከል፤ተጫዋች መሆን እና ቅድመ እይታን ማስተካከል፡፡
- መስራት እንደምትችሉ እራሳችሁን ማሳመን፡፡
- ስለራሳችሁ ጥሩ ስሜት እንዲሰማችሁ ከሚያስችሉ ሰዎች ጋር ጊዜአችሁን አሳልፉ፡፡

**ፅብረቃዊ ተግበር 1.6** በቡድን ተወያዩ

ለራስ የሚሰጥ ግምት/ዋጋን ለማጎልበት የሚረዱ ዘዴዎችን እንዴት አያችኋቸው?

## 1.4. ለራስ ግምት/ዋጋ መስጠት ያለው ጠቀሜታ

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

* ኑሮአችሁን ለማሻሻል ለራስ ግምት/ዋጋ መስጠት እንዴት ይረዳችኋል?
* በትምህርታችሁ ስኬታማ እንድትሆኑ ለእራስ ዋጋ መስጠት የሚኖረዉን ሚና ዘርዝሩ።

ለራስ ዋጋ መስጠት እናንተ ስለእራሳችሁ ጥሩ አስተሳሰብ እና ስሜት እንዲኖራችሁ ከማስቻሉ በተጨማሪ ራሳችሁን እንድታዉቁ፤ ራሳችሁን እንድትቀበሉ እና እንድታከብሩ ያደርጋችኋል። ራሳችሁን ስታዉቁ የራሳችሁን ደካማና ጠንካራ ጎን ትረዳላችሁ። እናንተ ራሳችሁን ስታከብሩ ራሳችሁን ባከበራችሁበት አኳኋን ልክ ሌሎችም ያከብሯችኋል። በራሳቸዉ የሚተማመኑ ሰዎች በራሳቸዉ ፈቃድ የተሻለ ውጤት ያላቸዉን አማራጮች መምረጥ ስለሚችሉ የተሻለ ኑሮ እንደሚኖራቸው ይሰማቸዋል።

**ፅብረቃዊ ተግባር 1.7**

ለራስ ዋጋ መስጠት ጠቀሜታዎች ላይ ተወያዩ

## 1.5. ተግዳሮትን የመቋቋም ጥንካሬ

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

- ለእናንተ ተግዳሮት ምንድን ነው?
- በህይወታችሁ ሊያጋጥማችሁ የሚችል ተግዳሮቶችን እንዴት ትቋቋማላችሁ?

በህይወት ውስጥ የሚያጋጥሙን ብዙ ተግዳሮቶች አሉ። አንዳንድ ሰዎች እነኝህን ተግዳሮቶች የመጋፈጥ ብቃት ሲኖራቸው ሌሎች ደግሞ አይኖራቸውም። ተግዳሮቶች ነባራዊ ግንዛቤያችንን በማጎልበት እድገትን ለማምጣት መልካም እድሎችን ሊፈጥሩ ይችላሉ።

ተግዳሮቶችን በምትጋፈጡበት ወቅት ውድቀት እንኳን ቢገጥማችሁ ከውድቀታችሁ መማር ከቻላችሁ እና አጋጣሚዉን በአግባቡ ከተጠቀማችሁ በተግዳሮቶች ውስጥ ጥንካሬንና ችግሮችን በቀላሉ የመፍታት ክህሎትን ታዳብራላችሁ። የትኛውም ተግዳሮት ሲያጋጥመን ለማለፍ እና ለመጋፈጥ ሊረዱን የሚችሉ መንገዶች ከዚህ በታች ቀርበዋል።

- ሁኔታዎችን መገምገም
- ያላችሁን ግብአት ማወቅ
- ያላችሁን ችሎታ እውቅና መስጠት

**ፅብረቃዊ መልመጃ 1.8**

ተግዳሮትን ለመጋፈጥ ሊረዱን በሚችሉ ክህሎቶች ላይ ተወያዩ።

## 1.6. ለራስ ዝቅተኛ ዋጋ/ግምት የመስጠት ተጽእኖዎች

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

- ለራስ ዝቅተኛ ዋጋ መስጠት መገለጫ ባህሪያት ምን ምን ናቸዉ?

- ለራስ ዝቅተኛ ዋጋ መስጠት መገለጫ ባህሪያት ምን ምን ናቸዉ?

ለራስ ዝቅተኛ ዋጋ የሚሰጡ ሰዎች የሚከተሉት ባህሪያት ይኖራቸዋል፡

- በራሳቸው ላይ እምነት የላቸውም፤
- የሆነ ነገር ከመጀመራቸው በፊት እራሳቸውን ከወዳቂዎች ተርታ ይመለከታሉ፤

- የራሳቸውን ስህተት ለመቀበል ይቸገራሉ፤
- መልካም ሰው ሊሆኑ እንደማይችሉ ያምናሉ፤
- ሌሎች ሰዎች ይስቁብኛል በሚል ፍራቻ የራሳቸዉን ፈጠራ ወይም እምቅ አቅም ለማሳየት አይሞክሩም፤
- በህይወታቸው እርካታ የላቸውም፤
- የመማር ፍላጎት ያጣሉ፤
- ብዙ ጊዜያቸዉን በብቸኝነት ያሳልፋሉ፤
- ሁልጊዜ ነቃፊ እና አማራሪ ይሆናሉ፤
- ስለ ሁሉ ነገር ይጨነቃሉ ግን ምንም አይሰሩም፤
- እኔ ይህን መስራት አልችልም” የሚል ዝንባሌ አላቸዉ፡፡

ፅብረቃዊ ተግባር 1.9

ለራስ ዝቅኛ ግምት/ዋጋ መስጠት በሚያስከትለው ችግር ዙሪያ ተወያዩ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ  ስለ ራስ ግምት/ዋጋ መስጠት ጽንሰ ሃሳብ አይተናል፡፡ ለራስ ዋጋ መስጠት የተለያዩ መገለጫ ባህሪያት አሉት፡፡ እነሱም በሌሎች ላይ ጥገኛ አለመሆን፤ በራስ መተማመን እና ራስን መግዛት ናቸዉ፡፡

ለራስ ግምት/ዋጋ መስጠት ጠቃሚ ነው፡፡ ምክንያቱም ለራስ ዋጋ መስጠት እናንተን ስለራሳችሁ ጥሩ እንድታስቡና ጥሩ ስሜት እንዲሰማችሁ በማድረግ የተሻለ ስራ እንድትሰሩ ያስችላችኋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለራስ ዋጋ መስጠት እናንተ ራሳችሁን እንድትቀበሉ፤ እንድታከብሩ እና እንድትተማመኑ ይረዳችኋል፡፡ በአዎንታዊ እና አሉታዊ ለራስ ዋጋ መስጠት ባህሪያት መካከል የሰፋ ልዩነት አለ፡፡

- ለራስ ግምት/ዋጋ መስጠት፡- አንድ ሰው ለራሱ የሚሰጠው ዋጋ/ግምት ማለት ነዉ፡፡
- ጥገኛ አለመሆን፡- አንድ ሰዉ ከሌሎች ምንም አይነተ ድጋፍ/እርዳታ ሳይፈልግ ያሰበውን ማሳካት ወይም መኖር መቻል ማለት ነዉ፡፡
- በራስ መተማመን፡- አንድ ሰዉ በራሱ ችሎታ ወይም አቅም ላይ በመተማመን ያሰበውን መፈጸም መቻል ማለት ነዉ፡፡
- ተግዳሮት፡- አንድ ሰዉ ያሰበዉ ግብ  እንዳያሳካ የሚከለክሉት ማንኛዉም አንቅፋት  ማለት ነዉ፡፡
- እራስን መግታት/ መቆጣጠር፡- ራሳችንን ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮችን ከማድረግ መቆጠብ ማለት ነዉ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ክፍል አንድ: የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በማንበብ አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እዉነት ትክክል ካልሆነ ደግሞ ሀሰት በማለት መልስ ስጡ፡፡**

1. ለራስ ግምት/ዋጋ መስጠት ማለት እኔ ትልቅ እና የምሰራውም ትክክል ነው ብሎ ማሰብ ነው፡፡
2. ጥገኛ ያልሆኑ ሰዎች ምንም አይነት ድጋፍ ከሌሎች ሰዎች የማይቀበሉ ናቸው፡፡
3. ተረጅውን ሰው ጥግኛ ስለሚያደርገው እርዳታ ማድረግ ጥሩ አይደለም፡፡

**ክፍል ሁለት: ከ ለ ስር የተዘረዘሩትን ቃላት ወይም ሀረጋት በ ሀ ስር ከተዘረዘሩት ትክክለኛ ፍቺ ጋር አዛምዱ**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. እራሳችንን የሚጎዱ ነገሮችን ባለማድረግ ለእራሳችን ደስታ መፍጠር፡፡ | ሀ. በራስ መተማመን |
| 2. በራስ አቅም እና ክህሎት ማመን፡፡ | ለ. ጥገኝነት |
| 3. ውሳኔ ለመወሰን በሌሎች ሰዎች ተጽዕኖ ስር መውደቅ. | ሐ. ጥገኛ አለመሆን |
| 4. በራስ ክህሎት ላይ ጥገኛ መሆን፡፡ | መ. እራስን መግታት |

**ክፍል ሦስት: የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማንበብ ከስራቸዉ ከተዘረዘሩት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛዉን መልስ ምረጡ፡፡**

1. ከሚከተሉት አንዱ የእናንተን በሌሎች ላይ ጥገኛ ያለመሆንን ክህሎት እንድታዳብሩ ይረዳችኋል፡፡

ሀ. እኔ የበላይ ነኝ ብሎ ለራስ እዉቅና መስጠት፡፡

ለ. ጥገኛ ያለመሆን ልምድን ማዳበር፡፡

ሐ. ከሌሎች ድጋፍ/እርዳታ መፈለግ፡፡

መ. እኔ አልችልም ብሎ ማመን፡፡

2. ከሚከተሉት አንዱ ዝቅተኛ ለራስ ግምት/ዋጋ የመስጠት ምልክት ነዉ?

ሀ. ባደረግነዉ ወይም ባሳካነዉ ነገር መርካት፡፡

ለ. አብዛኛዉን ግዜ በብቸኝነት ማሳለፍ፡፡

ሐ. እኔ እችላለሁ ብሎ ማሰብ፡፡

መ. ደካማ ጎንን ሁልጊዜ ማወቅ፡፡

3. ከሚከተሉት አንዱ በራሱ የሚተማመን ሰዉ አይደለም፡፡

ሀ. የሌሎችን ሰዋች ሀሳብ እና ነቀፌታ መቀበል፡፡

ለ. አዲስ አስተሳሰብ ይዞ ለመምጣት ድፍረት መኖር፡፡

ሐ. ሌሎች ሰዎች ሀሳባቸውን እና እምነታቸዉን በነጻነት እንዲናገሩ ማዳመጥ፡፡

መ. ማጭበርበር

4. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች አንዱ ስለ ጥገኝነት ትክክል ነዉ፡፡

ሀ. ጥገኝነት ካለ ምንም ድካም ለመኖር ጠቃሚ ነዉ፡፡

ለ. የጥገኝነት አስተሳሰብ ለበታችነት ስሜት ይዳርገናል፡፡

ሐ.ጥገኝነት ለማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገት ዋና መሳርያ ነዉ፡፡

መ.ጥገኝነት የመቻቻል አካል ነው፡፡

5. ከሚከተሉት አንዱ ለራስ ግምት/ዋጋ መስጠት መገለጫ ባህሪ አይደለም፡፡

ሀ. በራስ መተማመን

ለ. እራስን መግታት/ መቆጣጠር

ሐ. ጥገኛ አለመሆን

መ. የአቻ ግፊት

# ምዕራፍ ሁለት

## ሰብአዊ መብቶችን መረዳት

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፡-**

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የሰብአዊ መብቶቸ ጽንሰ-ሀሳብ ትናገራላችሁ፤
- በመብቶች እና ኃላፊነቶች መካከል ያለዉን የእርስ በርስ ግንኙነትን ትለያችሁ፤
- የሰብአዊ መብቶች ማክበር አስፈላጊነትን ተገልጻላችሁ፤

### መግቢያ

መብት ማለት ማንም ሊወስደዉ የማይችል በህግ የተሰጠ ዕዉቅና ማለት ነዉ፡፡ ይኸውም ሰው እንዲያደርግ ወይም እንዲኖረው የሚፈቅድ ደንብ ወይም ህግ ነው፡፡ መብቶች በህግ ሲቀመጡ ህጋዊ ከለላ ይኖረቸዋል፡፡ ሰብአዊ መብቶች ለሰው አስፈላጊ ናቸው፡፡ መብቶቹም ሊታዩ የሚችሉት በማህበረሰቡ በሁሉም ደረጃ በሚገኝ የሰዎች ግንኙነት ማለትም በቤተሰብ፤ በህብረተሰብ፤ ትምህርት ቤት እና ስራ ቦታ ነው፡፡ በመሆኑም ሰው ሊረዳቸው ይገባል፡፡ እነዚህን መረዳት ሠላምን፤ ፍትህን እና ማህበራዊ ደህንነትን ለማሳደግ ይረዳል፡፡

## 2.1. የሰብኣዊ መብቶች ምንነት

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

- ሰብአዊ መብቶች ምንድን ናቸው?
- ቢያንስ ሦስት የሰብአዊ መብት ምሳሌዎችን ጥቀሱ




ስዕል 2.1 ስለ ሰብዓዊ መብቶች ግንዛቤ መፍጠር

ሰብአዊ መብት ማለት ሰው በመሆናችን ለሁላችን የተሰጠ መሰረታዊ መብት ነው፡፡ ማንኛውም ሰው በዘሩ ፣ በጾታ ፣ በሃይማኖት ፣ በጎሳ ፣ በብሄር እና ፖለቲካዊ አመለካከት ልዩነት ሳይደረግበት የሚጎናፀፋቸው ናቸው፡፡ በህይወት የመኖር ፣ የነጻነት ፣ የእኩልነት ፣ የደህንነት ፣ ከባርነት ነጻ መሆን ፣ የአመለካከት እና የሀሳብ ነፃነት ፣ የመስራት እና የመማር መብቶች የተለመዱ የሰብአዊ መብት ምሳሌዎች ናቸው፡፡ የደህንነት መብት የሚያመለክተው ማንም ሰው ለአካላዊ እና ሞራላዊ ጉዳት እንዳይዳረግ ነው፡፡ ከተወሰኑ የህግ ፍርደኞች በስተቀር እነዚህን መብቶች ማንም ማጣት የለበትም፡፡

**2.1 የጽብረቃ ተግባር**

ባዶ ቦታውን ሙሉ፡፡

1. ሰብአዊ መብቶች ለእኛ ለሁላችንም-------------------በመሆናችን ምክንያት የተሰጡ ናቸዉ፡፡

2 ----------መብት ሰው አካላዊ እና ስነ ልቦናዊ ጥቃት ሊደርስበት እንደማይገባ ያመለክታል፡፡

## 2.2. ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ጠቀሜታ

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

- ሰብአዊ መብቶችን ማክበር ለህብረተሰቡ ምን አስተዋፅኦ አለው?
- የሌሎችን መብት በማክበር እና ሌሎች እንዲያከብሩ በመጠበቅ መካከል ግንኙነት አለው?
- በትምህርት ቤትእና በክፍልህውስጥ ሰብአዊ መብቶችን የማክበርን አስፈላጊነት አብራሩ።

ሁሉም የሰው ልጆች ነጻ ሆነው የተወለዱ ሲሆን በክብር እና በመብት እኩል ናቸው። ሰብአዊ መብቶች ሁላችንን ለመጠበቅ ቁልፍ መሣሪያዎች ናቸው። እንደዚሁም በማህበረሰባችን ውስጥ ቁልፍ እሴቶች ናቸው። እሴቶቹም እንደ ሰላም ፣ ፍትሃዊነት ፣ ክብር ፣ እኩልነት እና መከባበር ናቸው። እኛ የምንናገርበት እና በሰላም ለመኖር የሚያስችል ኃይል ይሰጡናል። ሰብአዊ መብቶችን ማክበር አስፈላጊ የሚሆነው፡-

- ✓ በስምምነት ለመኖር፣
- ✓ ተግባራትን በሰላም ለማከናወን እና ከጭቆና የጸዳ ማህበረሰብ ለመፍጠር።

መብቶቻችንን በእለት ተእለት እንቅስቃሴያችን ውስጥ ይጠብቁናል። ለምሳሌ፡-

- ✓ ሀሳብን በነጻነት ለመግለጽ ፣
- ✓ ትምህርት ለማግኘት፣
- ✓ መጫወት እና ከበደል ነጻ ለመሆን።

**ፅብረቃዊ ተግባር 2.2**

ዐረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" እና ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡

1. ሰብአዊ መብቶች ሀሳብን በነጻነት እንድንገልጽ እና በሰላም እንድንኖር ይረዱናል.፡፡
2. ሁሉም የሰው ልጆች የተወለዱት ነፃ፤ ክቡር እና እኩል ሁነዉ ነዉ፡፡
3. በሰላም ለመኖር ሰብአዊ መብቶችን ማክበር አስፈላጊ ነው፡፡
4. ሰብአዊ መብቶችን ማክበር በብዙ የእለት ተእለት ህይወታችን ውስጥ ይጠብቁናል፡፡

## 2.3. ሰብአዊ መብቶች እና ኃላፊነት

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

- መብቶች እና ግዴታዎች ምን አይነት ግንኙነቶች አላቸው?
- ያለ ግዴታ መብት ካላችሁ ምን ይፈጠራል?

መብቶች ከኃላፊነት ጋር አብረው ይሄዳሉ፡፡ ሰብአዊ መብቶች ሰዎች በጋራ የሚጋሯቸው የመብቶች እና የኀላፊነቶች ስብስብ ነው፡፡ ግለሰቦች መብቶቻቸውን ሲጠቀሙ የሌሎች ግለሰቦችን መብት ማክበራቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ለምሳሌ፡- አንድ ሰው በነጻነት የመናገር መብቱን ሲጠቀም የሌሎችን መብት በማክበር መሆን አለበት፡፡ በሌላ በኩል አንድ ሰው የመናገር ነፃነቱን ተጠቅሞ ሌሎችን መሳደብ አይችልም፡፡ መንግስት ሰዎች የሌሎችን መብት ሳይጥሱ በመብታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ ልዩ ኃላፊነት አለበት፡፡ መብቶች ሰዎች ሊኖሯቸው የሚፈልጓቸው የይገባኛል ጥያቄዎች ናቸው፡፡

ከመብቶቻችሁ ጋር እናንተም ያላችሁን ኃላፊነት የሚያመለክቱ አንዳንድ ምሳሌዎች ከታች ተዘርዝረዋል፡፡

መብቶች-

- ✓ ደህንነት የመሰማት መብት፤
- ✓ የመኖር መብት፤
- ✓ ምግብ የማግኘት መብት፤
- ✓ ትምህርት የማግኘት መብት፤

ኃላፊነቶች፡-

የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉባችሁ

- ✓ ቤተሰቦቻችሁን እና ታላላቆቻችሁን ማዳመጥ እና መታዘዝ ፤
- ✓ የሌሎችን ደህንነት አለመንካት፤
- ✓ ቤተሰቦቻችሁን እንደ እድሜያችሁ እና እንደ ችሎታችሁ ማገዝ፤
- ✓ እናንተን ወይም ሌሎችን ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮችን አለማድረግ፤
- ✓ ክፍላችሁን እና በቤታችሁ ዙሪያ ያሉትን ቦታዎች ንፁህ ማድረግ፤
- ✓ ለእናንተ ጠቃሚ የሆኑ ምግቦችን መመገብ፤
- ✓ ጊዜያችሁን በአግባቡ መጠቀም፤ በትምህርት ቤታችሁ በትጋት መስራት፤

መብቶች እና ኃላፊነቶች የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡ ኃላፊነታችሁን አለመወጣት እናንተን ወይም ሌሎችን ይነካል፡፡ ለምሳሌ፡- ለወላጆቻችሁ መታዘዝ እና መርዳት ከጓደኞቻችሁ ጋር መጫወት እንድትችሉ

ያግዛችኋል፡፡ እንደዚሁም ቆሻሻ ስታዩ ካነሳችሁት አካባቢያችሁ ንጹህ ይሆናል፡፡ ምግብ ከመብላታችሁ በፊት እጃችሁን ከታጠባችሁ ጤነኛ ትሆናላችሁ፡፡ የሌሎችን መብቶች መጣስ የለባችሁም፡፡ ምክንያቱም በመብት እና ግዴታ መካከል ያለው ግንኙነት የተመሰረተው በዚህ መንገድ ነውና፡፡

## የቡድን ውይይት ተግባር፡-

“መብቶች እና ግዴታዎች የአንድ ሳንቲም ሁለቱ ገጽታዎች ናቸው” የሚለው አገላለጽ ምንን ያሳያል?



ስዕል 2.2 ተማሪዎች ክፍላቸዉን ሲያጸዱ

## ፅብረቃዊ ተግባር 2.3

ከዚህ በታች ያለውን ሠንጠረዥ በመልመጃ ደብተራችሁ በመገልበጥ ባዶ ቦታዎችን ሙሉ፡፡

- ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ እና ባዶ ቦታዎች ላይ ተጨማሪ መብቶችና ሀላፊነቶችን ጻፉ፡፡ ከታች ምሳሌ ቀርቦላችኋል፡፡

| ተ.ቁ | መብት | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | መጫወት | የትምህርት ቤቱን ንበረት መጠበቅ፣ |
| 2 | | |
| 3 | | |
| 4 | | |
| 5 | | |

## 2.4. የሰውን ክብር ማክበር

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

* ክብር ምንድን ነው?
* የክፍል ጓደኞቻችሁን ታከብራላችሁ?



ስዕል 2.3 ለሰዉ ክብር ማሳየት

ክብር ራሳችሁን እና ሌሎችን የምታከብሩበት እና ዋጋ የምትሰጡበት ሁኔታ ማለት ነው። ይኸውም ለራስ ዋጋ መስጠት፤ ራስን ማድነቅ፤ ለራስ ጥንቃቄ ማድረግ፤ እራስን ማክበር እና በራስ መተማመንን ያካትታል። ሰብዓዊ ክብር ማለት የአንድ ሰው የመከበር፣ ዋጋ የመሰጠት፣እና በጥሩ ሁኔታ የመገልገል መብት ማለት ነው። የሰው ልጅ ክብር የእያንዳንዱ ሰው እውቅና እና ዕድሜ፣ ችሎታ፣ የኑሮ ደረጃ፣ ጾታ፣ ቀለም፣ ዘር፣ ወዘተ ሳይለይ በአክብሮት የሚስተናገድበት ሁኔታ ነው። በጥቅሉ ራሳችን መስተናገድ በምንፈልገው ሁኔታ ሌሎችን ማስተናገድ ማለት ነው። እናንተም የራሳችሁን፤ የቤተሰቦቻችሁን፤ የጓደኞቻችሁን እና የጎረቤቶቻችሁን ክብር መጠበቅ አለባችሁ። ከዚያም እነሱም የእናንተን ክብር ይጠብቁላችኋል።

ሰብአዊ ክብር በተለምዶ እንደ ሰብአዊ መብቶች ግብረ-ገባዊ መሠረት ይቆጠራል፡፡ የሰውን ክብር ከሚጥሱ ተግባራት መካከል ስድብ፣ ማህበራዊ መገለል፣ ረሃብ፣ ወንጀል፤ ጦርነት እና የጉልበት ብዝበዛ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ሌሎችን በአክብሮት የምንይዝባቸው አንዳንድ መንገዶች አሉ፡፡ እነሱም፡-

- ✓ ለእያንዳንዱ ሰው መሰረታዊ ክብር እውቅና መስጠት፤
- ✓ ለእያንዳንዱ ሰው የህይወት ሁኔታ ርህራሄ ማሳየት፤
- ✓ የሌላውን አስተያየት እና ግብዓት ማዳመጥ እና ማበረታታት፤
- ✓ የሌሎች ሰዎችን አስተዋፅዖ እዉቅና መስጠት፣ ወዘተ...

**ፅብረቃዊ ተግባራት 2.4**

ባዶ ቦታዎችን ሙሉ

1. ____________ ማንኛውም ሰው ሊሰጠው የሚገባው እውቅና ነው፡፡

2. የሰውን ክብር የሚጋፉ ተግባራትን ዘርዝሩ፡፡ __________________፣ ________ ______________፣ ________________________፣ _________________________፣

## 2.5. የህጻናትን መብት ማክበር

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

- ህጻናት ሊኖሯቸው የሚችሏቸውን አንዳንድ ልዩ መብቶች ጥቀሱ፡፡
- በህጻንነታችሁ ምን መብቶች አግኝታችሁ ነበር?

በኢትዮጵያ የቤተሰብ ህግ መሰረት እድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ሰው እንደ ህፃን ይቆጠራል፡፡ በልጅነታችሁ ደህንነትን ለማራመድ መብት አላችሁ፡፡

እያንዳንዱ ህጻን የመማር፣ በጤንነት መኖር፣ የመጫወት፣ ወዘተ መብት ሊኖረው ይገባል፡፡ የሚኖራቸዉ መብቶችም በሚከተሉት ነጥቦች ውስጥ ይጠቃለላሉ፡፡ ህፃናት ተመሳሳይ መብቶች አሏቸው፡፡ በፆታ፣ በዘር፣ በቋንቋ፣ በእድሜ ወይም በሃይማኖታቸዉ ምክንያት ለችግር መዳረግ የለባቸዉም፡፡ የሚከተሉትን መብቶች የማግኘት መብት አላቸዉ፡-

- ✓ የህክምና እና የጤና እንክብካቤ፣
- ✓ ነፃ መሰረታዊ ትምህርት፣
- ✓ የእረፍት ጊዜ፣
- ✓ በባህላዊ እና ጥበባዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የመሳተፍ እድል፣
- ✓ መረጃ የማግኘት፣ ሃሳባቸውን የመግለጽ ነፃነት፣
- ✓ ጥሩ አስተዳደግ፣
- ✓ ከጦርነት ልዩ ጥበቃ የማግኘት፣
- ✓ የጉልበት ብዝበዛ ስራ እና ከኢ-ሰብአዊ አያያዝ የመጠበቅ፡፡

እንዲሁም ከወላጆቻቸው ጋር የመኖር እና እናት እና አባታቸው ቢለያዩ እንኳን ከሁለቱም ጋር የመገናኘት መብት አላቸው፡፡

አካል ጉዳተኛ ህጻናት የሚከተሉት መብት አላቸው፡፡ ልዩ ድጋፍ የማግኘት እንዲሁም በህብረተሰቡ ንቁ ሚና የመጫወት መብት አላቸው፡፡ ህጻናት በህይወታቸው ስኬታማ እንዲሆኑ ከሚረዱት ምርጥ መንገዶች አንዱ እነሱን ማስተማር ነው፡፡



ምስል 2.4፡ ተማሪዎች ደስተኛ ሆነው በትምህርት ቤት ውስጥ ሲጫወቱ

ፅብረቃዊ ተግባራት 2.5

1. የህጻናትን መብት የማክበር ጥቅሞች ምን ምን ናቸው?

2. በማህበረሰብ ውስጥ የህጻናትን መብቶች የማክበር ግዴታዎች እንዴት ይተገበራሉ?

## 2.6. የሴቶችን መብት ማክበር

የማነቃቂያ ጥያቄዎች

- ሴቶች በየትኛውም ቦታ ቢሆን እንደ ወንዶች ማንኛውንም ሥራ መሥራት ይችላሉ በሚለው ሐሳብ ትስማማላችሁ?
- ከሴቶች መብቶች አንዳንድ ምሳሌዎችን መጥቀስ ትችላላችሁ?

የሴቶችን መብት ማክበር አንዱ የሞራል እሴታችን ነው:: ይህን መቀበል እና ማክበር አስፈላጊ ነው:: የፆታ እኩልነትን ማክበር አለብን:: ማንኛውም ዜጋ የፆታ አድሎአዊነትን መታገል አለበት:: የሴቶች እና የወንዶች እኩልነትን መቀበል እና መደገፍ ይጠበቅበታል:: ሁሉም ወንዶች ያላቸው መብቶች የሴቶችም መብቶች ናቸው:: የትምህርት፣ የመሬት ባለቤትነት፣ የመኖሪያ እና የንብረት ባለቤትነት መብቶች ለሴቶች አስፈላጊ ናቸው:: እኩልነት እና የደህንነት መብቶች ለሴቶች እና ለልጆች አስፈላጊ ናቸው:: የሴቶች መብት ማክበር ማለት የእናቶችን እና የእህቶችን መብት መቀበል እና ማክበር ማለት ነው::





ምስል 2.5: ሴቶች የተለያዩ ሥራዎች ሊኖራቸው ይችላል

ፅብረቃዊ ተግባር 2.6

ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ፡፡

1. የሴቶችን መሰረታዊ መብቶች ዘርዝሩ፡፡

2. ከሥርዓተ-ፆታ አድልዎ ጋር መታገል ያለበት ማን ነው?

## 2.7. የአካል ጉዳተኞችን መብት ማክበር

የማነቃቂያ ጥያቄዎች

* "አካል ጉዳተኛ" ማለት ምን ማለት ነው?

* ወደ አካል ጉዳተኝነት የሚያመሩ ሁኔታዎችን አብራሩ፡፡



ምስል 2.6፡ አካል ጉዳተኞች የትምህርት መብት አላቸው

**አካል ጉዳተኝነት፡-** በሰው ልጅ እንቅስቃሴ፣ የአካል ብቃት፣ ጉልበት ወይም ብልህነት ላይ ተጽዕኖ የሚያስከትል ማለት ነው፡፡ አካል ጉዳተኞች እንደ ማንኛውም ሰው ሙሉ ክብር እና ተመሳሳይ መብቶች አላቸው፡፡ የአካል ጉዳተኞች ከቤተሰብ፣ ከመንግስት፣ ከሰብአዊ ድርጅቶች ደጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

እንዲሁም ትምህርት የማግኘት መብት አላቸው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ማየት የተሳናቸው ሰዎች የብሬይል መጽሐፍ ማግኘት አለባቸው፡፡ ሁሉም ሕንፃዎች፣ ዕቃዎች፣ ምርቶች፣ መገልገያዎች፣ መሠረተ ልማቶች፣ ቴክኖሎጂዎች እና አገልግሎቶች መነደፍ ያለባቸው ለአካል ጉዳተኞች ምቹ እና ተደራሽ በሚሆኑበት መንገድ ነው፡፡ አካል ጉዳተኝነት አብሮ በመወለድ፤ በአካል ጉዳት ወይም በህክምና ስህተት ሊከሰት ይችላል፡፡

**ፅብረቃዊ ተግባር 2.7**

- የአካል ጉዳተኞች መብቶችን ዘርዝሩ?

**ሁኔታ**

ሰሚራ የመስማት ችግር አለባት፡፡ በዚህም ምክንያት ክፍል ውስጥ ለመሳተፍ በጣም ተቸግራለች፡፡ ይህንን በመመልከት አስተማሪዎቿ ከክፍሉ ፊት ለፊት እንድትቀመጥ አድርገዋታል፡፡ ትምህርት ቤቱም አጋዥ የማዳመጫ መሣሪያ ረድቷታል፡፡ በተመሳሳይም የክፍል ጓደኞቿ አብዛኛውን ጊዜ ፍቅር እና አክብሮት ያሳዩዋታል፡፡ በዚህም ምክንያት ውጤታማ ሆና ከፍተኛ ውጤት አስመዝግባለች፡፡

**ፅብረቃዊ ተግባራት 2.8**

1. ስለ ሰሚራ ስኬት ምን ይሰማችኋል?
2. ሰሚራ ምን አይነት ድጋፍ ታገኛለች?
3. ሰዎች ሰሚራን እንዴት ሊረዷት ይችላሉ?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ሰብአዊ መብቶች ለሰው ልጅ ሁሉ የሚሰጡት ሰው በመሆኑ ነው፡፡ ለምሳሌ በህይወት የመኖር፣ የእኩልነት እና የደህንነት መብቶች ሰው በመሆኑ የተሰጡ ሰብአዊ መብቶች ናቸው፡፡

መብቶች እና ኃላፊነቶች የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡ መብቶቻችንን ስንጠቀም ግዴታዎቻችንን መርሳት የለብንም፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው መብቱን ሲጠቀም፣ እሱ ወይም እሷ የሌላውን ሰው መብት መጣስ የለባቸውም፡፡ ህጻናት ሁሉ መሠረታዊ መብቶች አሏቸው፡፡ እነዚህ መብቶች ሰዎች በሰላም ለመኖር ያስችላቸዋል፡፡ እነሱን ማክበር ኢ-ፍትሃዊ አያያዝን ወይም ጭቆናን ማስወገድ ማለት ነው፡፡ የአካል ጉዳተኞች መብቶች፣ የህጻናት መብቶች እና የሴቶች መብቶች መከበር አለባቸው፡፡ አካል ጉዳተኝነት በማንኛውም ሰው ላይ ሊከሰት የሚችል ክስተት ነው፡፡ ይህ ክስተት ተፈጥሯዊ ወይም ሰው ሰራሽ ሊሆን ይችላል፡፡ የአንድን ግለሰብ መብት ማክበር በማህብረተሰብ ደረጃ ጠቀሜታ አለው፡፡ የፖሊስ መሥሪያ ቤቶች እና ፍርድ ቤቶች የሰብዓዊ መብቶችል የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለባቸው ድርጅቶች ናቸው፡፡

**ቁልፍ ቃላት፡-**

- መብቶች፡- ለሁሉም የሰዉ ልጅ የተሰጡ ህጋዊ ጥበቃ ያላቸዉ መብቶች ናቸው፡፡
- ሰብአዊ መብት- የሰዉ ልጅ ሰው በመሆኑ ብቻ የሚያገኛቸው መብቶች ናቸዉ፡፡
- አካል ጉዳተኝነት፡- የሰውን ልጅ የሚጎዳ የረዥም ጊዜ የአካል እክል ነው፡፡
- ክብር፡- አንድ ሰው ሰው በመሆኑ የሚያገኘው ክብር እና ዋጋ ነው፡፡

## የምዕራፉ ክለሳ መልመጃዎች

እነዚህን የክለሳ መልመጃዎች ጥያቄዎች በመለማመጃ ደብተራችሁ ውስጥ በመጻፍ መልሱ።

**ክፍል አንድ. አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" እና ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት ጻፉ**

1. መብት ለአንድ ሰው አንድ ነገር እንዲኖረው ወይም እንዲያደርግ የተሰጠ የሞራል ወይም የህግ ጥያቄ ነው።

2. ከእያንዳንዱ መብት ጋር አብረው የሚሄዱ ኃላፊነቶች አሉ።.

3. ልጆች ከመብታቸው በተጨማሪ አንዳንድ ግዴታዎች አሏቸው።

4. ሰዎች የፈለጉትን የመናገር መብት አላቸው።

5. ሁሉም ሰዎች እኩል መብት አላቸው።.

6. መብቶች እና ኃላፊነቶች የማይነጣጠሉ ናቸው።.

**ክፍል ሁለት፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።**

1. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ለአካል ጉዳተኛ ሊሰጥ የሚገባው ድጋፍ አይደለም።

   ሀ. ፍቅር እና እንክብካቤ

   ለ. መገለልና መድልዎ

   ሐ. የትምህርት ቁሳቁሶችን ማቅረብ

   መ. የእኩልነት መብታቸውን ማክበር፤

2. ________________ የሰው ልጅ ልዩ ነገር እንዳለው እውቅና መስጠት ነው።

   ሀ. ሰብአዊ ክብር ለ. የሴቶች መብት

   ሐ. የአካል ጉዳተኝነት መ. የህጻናት መብቶች

3. ______________የሴቶችን መሰረታዊ መብትና ክብር የሚነካ ተግባር ነው፡፡

ሀ. ትዳር

ለ. በማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ

ሐ. የወንዶችን ሥራ መሥራት

መ. የሴት ብልት ግርዛት

4. ከሚከተሉት ውስጥ የአካል ጉዳት የማያስከትለው የትኛው ነው?

ሀ. በሽታ ሐ. ግጭት እና ጦርነት

ለ. የምግብ እጥረት መ. የአካል ጉዳተኛ ከሆኑ ልጆች ጋር መጫወት

5. ______________ ከሴቶች መብት ውስጥ አይደለም፡፡

ሀ. የመሬት ባለቤትነት መብት

ለ. የመኖሪያ ቤት ባለቤትነት መብት

ሐ. የንብረት ባለቤትነት መብት

መ. በሌሎች የበላይ የመሆን መብት

ክፍል ሦስት፡ ባዶ ቦታውን ይሙሉ፡፡

1. ________________አንድ ሰው ሰው በመሆኑ የሚያገኘው ዋጋ ነው፡፡

2. ________________ውጤት ላይ ለመድረስ የተወሰኑ ተግባራትን የመፈጸም ግዴታ ነው፡፡

ክፍል አራት፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ፡፡

1. በእርስዎ ማህበረሰብ ውስጥ አካል ጉዳተኞች ምን አይነት ድጋፍ ይፈልጋሉ?

2. በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ያሉ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ምን ዓይነት ድጋፍ ማግኘት አለባቸው?

# ምዕራፍ ሦስት

## ሰላም

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች:-**

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- የሰላምን ፍች ታብራራላችሁ።
- የሰላምን ጠቀሜታ ትገልጻላችሁ።
- የሰላም ማስፈኛ መንገዶችን ትዘረዝራላችሁ።
- የራሳችሁን ሰላማዊ የግጭት መፍቻ አቅምና ዘዴ ትገልፃላችሁ።

### መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ስለ ሰላም ጽንሰ-ሀሳብ ጠቀሜታ ትማራላችሁ። ሰላም ለማንኛዉም ግለሰብ እና የማህበረሰብ እድገት የማዕዘን ድንጋይ ነዉ። ሰላም ማህበረሰባዊ ውህደትን እና መረጋጋትን በማምጣት ማህበረሰባዊ እድገትን ያፋጥናል። በዚህም ምክንያት ሰላም የተረጋጋ ማህበረሰብ ለመፍጠር እንዲሁም እድገትን ለማፋጠን እንደ ቅድመ ሁኔታ ይታያል። ሰላም እና ስምምነት በቤተሰብ ሆነ በግለሰብ ደረጃ የኢኮኖሚ አቅማችንን ለማሳደግ እና ድህነትን ለመቀነስ ይረዳናል። ግለሰባዊ እና ማህበረሰባዊ ኑሮአችንን በማበልጸግ ብዝሀነትን እንድናቅፍ ይረዳናል። የሰላም እጦት በማህበረሰቡ የኢኮኖሚ እድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል።

## 3.1 ሰላም

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

- ሰላም ምንድን ነው?
- ሰላም እንዴት ይጠበቃል?

ሰላም ብጥብጥ እና ጠላትነት የሌለበት የማህበረሰባዊ ጓደኝነት እና ስምምነት ጽንሰ ሀሳብ ነዉ። ከማህበረሰባዊ እይታ አንጻር ሰላምን ስናየዉ አብዛኛዉ ሰዉ የሚረዳው በግለሰቦች ወይም በቡድኖች መካከል የሚደረግ ግጭት እና የቀጥታ ጦርነት አለመኖር አድርጎ ነዉ። የሰላምን ትርጉም ሰፋ አድርገን ስናየዉ ግን መዋቅራዊ ወይም በተዘዋዋሪ ሁከት ፣ ድህነትና ኢፍትሃዊነት አለመኖር ማለት ነዉ።

**ፅብረቃዊ መልመጃ 3.1**

1. በክፍል ዉስጥ ለሚደረግ ውጤታማ ለሆነ ትምህርት ሰላም አስተዋጽኦ አለዉ?
2. ሰላም ባይኖር ምን ይከሰታል?

**የሚከተለውን ተረት አንብቡና እና ተከታዩን ጥያቄዎች መልሱ።**

ግርማ የ4ኛ ክፍል ትምህርቱን በአዋሾ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እየተማረ ነበር። በቅርብ ጊዜ በክልሉ ለሚደረገው የንግግር ውድድር ተሳታፊ እንዲሆን ተመርጧል። ከትምህርቱ በኋላ ለአስተማሪዎቹ እና ለትምህርት ቤት ጓደኞቹ ንግግሩን ያቀርባል። ይሄን የሚያደርገዉም የንግግር ችሎታዉን ለማሻሻል የሚረዳውን አስተያየት ከተመልካቾቹ ለመቀበል በማሰብ ነዉ።

የንግግሩ ርዕስ ስለ ሰላም ሲሆን ንግግሩን በሚያቀርብበት ጊዜ ንግግሩን የሚገመግሙ እና አስተያየት የሚሰጡ አምስት የተከበሩ ዳኞች ተሰይመዋል፡፡ የእርሱ ንግግርም እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

የተከበራችሁ መምህራን እና ዉድ ጓደኞቼ! ንግግሬን የማቀርበው ስለ “ሰላም” ሲሆን አላማየም በክልል ደረጃ ለሚደረገው የንግግር ውድድር ለመሳተፍ ነዉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ “ሰላም” የአለምን ትኩረት ይዟል፡፡ ሰላም ህይወት ላለዉ ሁሉ አስፈላጊ ነዉ፡፡ ሰላም የደህንነታችን እና የደስታችን መሰረት ነዉ፡፡ ትዕግስት፤ መቻቻል፤ እርካታ እና ሌሎችን የመርዳት ዝንባሌ ዉስጣዊ ሰላም እንዲኖረን ይረዱናል፡፡ ሰላም በንግግር የምናገኘው ወይም ከሌሎች ሰዎች የምንጠብቀዉ ነገር አይደለም፡፡

ሰላም ለህሊናችን እና ለሰዉነታችን ትኩረት በመስጠት የምናገኘዉ የተለየ ደስታ ነዉ፡፡ የትኛውም ሰዉ ይህን አይነት ደስታ ማግኘት ይፈልጋል፡፡ እዉነተኛ ሰላም የውስጣዊ እና የዉጫዊ ሰላም ዉህደት ነዉ፡፡ የኛ እሴት፣እሳቤ እና ድርጊት ለውስጣዊ ሰላም አስተዋጽኦ አላቸዉ፡፡ ለውስጣዊ ሰላማችን ትኩረት መስጠት አለብን፡፡ ሰላም ለሁሉም! ምን ግዜም ሰላም፡፡ ዉስጣዊ ሰላም ሰላምን ለመጠበቅ እና ለውጫዊ ሰላም ለማስፋት አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም ሰላም ለቤተሰብም ሆነ ለግለሰብ ሰላማዊ ህሊና መጠበቅ በእኩል አስፈላጊ ነዉ፡፡ ሰላም ለማህበረሰብ ደህንነትም አስፈላጊ ነዉ:: የተፈጥሮ ዓለም ሰላሟን በምታጣበት ጊዜ እኛም ለተለያዩ መከራዎች እንዳረጋለን፡፡ ሰላምን ለመጠበቅ ጥረት ማድረግ አለብን፡፡ ሰላምን የሚያደፈርሱ እና ለብጥብጥ የሚዳርጉን ነገሮችን ማድረግ የለብንም፡፡ እናንተ በሀገራችን ውስጥ በተከሰተው የብጥብጥ እና የሰላም ማጣት መጥፎ ቱርፋቶች ልምዱ ሊኖራችሁ ይችላል፡፡

ግለሰቦች፤ ማህበረሰቦች እና ዜጎች ሰላም ያስፈልጋቸዋል፡፡ እያንዳንዱ ሰዉ ኢትዮጵያ ሰላም እንድትሆን ይፈልጋል፡፡ እያንዳንዳችን በጋራ በሀገራችን ሰላም እንዲሰፍን እና እድገቷ እንዲረጋገጥ የበኩላችንን አስተዋፅኦ ማድረግ አለብን፡፡ አመሰግናለሁ፡፡



ስዕል 3.1: ተማሪ ግርማ ስለ ሰላም ዘገባ ሲያቀርብ

**ፅብረቃዊ መልመጃ 3.2:**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ሰጡ፡፡

1. የመናገር ጥበብን እንዴት ማሳደግ ይቻላል?
2. ሰላም ምንድን ነዉ?
3. ሰላምን እንዴት ማስተላለፍ ይቻላል?
4. እንዴት ሰላም መሆን እንችላለን?

## 3.2. የሰላም ጠቀሜታዎች

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

- ቢያንስ ሶስት የሰላም ጥቅሞችን ዘርዝሩ::
- ያለ ሰላም መኖር ይቻላል? ጉዳዩን በግለሰብ፣ በቤተሰብ ፣ በማህበረሰብ እንዲሁም በሀገር ደረጃ ሰፋ አድርጋችሁ አስቡት::

ሰላም ለእያንዳንዱ ግለሰብ እና ማህበረሰብ እድገት የማዕዘን ድንጋይ ነዉ:: ሰላም እና ስምምነት በሕይወት ለመኖር እና ልማት ለማረጋገጥ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው:: ሰላም የሰዎችን መቻቻል እና ሰላማዊ አብሮ መኖርን ያበረታታል:: ሰላም በሰዎች መካከል ትብብር በመፍጠር የንግድ ግንኙነቶችን ያጠናክራል:: በቤተሰብ እና በግለሰባዊ ደረጃም ሰላም ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ደህንነትን ለማስጠበቅ ይረዳል:: ሰላም ልዩነትን እንድንቀበል እና በተቻለ መጠን እርስ በርሳችን እንድንደጋገፍ ስለሚረዳን ሰላም የማህበረሰባችንን እና የግል ሕይወታችንን ያበለጽጋል::

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

- አራት ወይም ሶስት ቡድን በመሆን በማህበረሰባችሁ እና በትምህርት ቤታችሁ ዉስጥ ሰላምን ለማጎልበት በሚረዱ ዘዴዎች ዙሪያ ተወያዩ::
- እንዴት?

## 3.3 ሰላምን በቤተሰብ እና በማህበረሰብ ማጎልበት

**ፅብረቃዊ መልመጃ 3.3**

1. ሰላም በትምህርት ቤት እና በክፍል ውስጥ ለመማር እንዴት ይረዳል?
2. ሰላም የሀገሮችን ወዳጅነት ለማምጣት እንዴት ይረዳል?

ሰላም ለቤተሰብ እና ለህብረተሰብ እድገት መሠረት ነው:: ስለዚህ በተለያዩ ደረጃዎች መተዋወቅ አለበት:: በኅብረተሰቡ ውስጥ ሰላምን ለማስፈን በግለሰቦች እና በመንግስት የሚተገበሩ የተለያዩ ስልቶች አሉ፡፡ እነሱም- ማህበራዊ ፍትህ፣ የሰብአዊ መብት ጥበቃ፣ መቻቻል፣ ውይይት፣ የግጭት አፈታት እና ትብብር ናቸው፡፡



ስዕል 3.2 ሰዎች በማህበራዊ ህይወት ሲተባበሩ

በተጨማሪም ቤተሰብ ለግለሰብ እድገትና ደስታ እንዲሁም ለህብረተሰብ ትብብር እና እድገት መሠረት ይጥላል፡፡ እንደ ህብረተሰብ ክፍል ቤተሰብ፡- እንደ ፍቅር፣ አንድነት፣ ርህራሄ፣ ፍትህ፣ አክብሮት እና ታማኝነት ያሉ በጎነቶችን በማበረታታት ሰላምን ለማጎልበት ቁልፍ መሣሪያ ነው፡፡ የቤተሰብ አባል እንደመሆናችሁ መጠን በቤት ውስጥ እንደዚህ ያሉ እሴቶችን መለማመድ ያስፈልጋል፡፡

## በቤተሰብ ውስጥ ሰላምን የሚያበረታቱ አንዳንድ ጠቃሚ ስልቶች

### 1. አክብሮትን ማበረታታት

ቤት የቤተሰብ አባላት በሰላም እና በስምምነት መኖር የሚችሉበት ቦታ ነው፡፡ በቤተሰብ አባላት መካከል ማንኛውንም አይነት የመናናቅ ምልክት በማስወገድ ቀልድ እና አስደሳች ጨዋታ የሞላበትን አካባቢ መፍጠር አለባችሁ፡፡ ወላጆች አንዳቸው ለአንዳቸው እንዲሁም በልጆቻቸው መካከል መከባበር እንዲኖር የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ማድረግ አለባቸው፡፡



ስዕል 3.3 የቤተሰብ አባላት እርስ በእርሳቸዉ ሲከባበሩ

## 2. አላሰፈላጊ ዉድድርን ማስወገድ

ብዙ ልጆች እርስ በእርስ መወዳደር ይወዳሉ፡፡ ጤናማ ያልሆነ ውድድር በቤተሰብ ውስጥ የግጭት እና ያለመግባባቶች ዋና ምንጭ ይሆናል፡፡ በተወሰኑ ጉዳዮች በስኬታችሁ ምክንያት ከሌሎች የላቀ ስሜት ሊሰማችሁ ይችላል፡፡ እያንዳንዳችሁ አንዳችሁ ሌላውን የምትደግፉበት ቤተሰባዊ ከባቢን ፍጠሩ፡፡ ይህ ደግሞ ጠንካራ ታማኝነት እና ፍቅርን ለማጎልበት ይረዳችኋል፡፡

## 3. አዎንታዊ ንግግሮች ወይም ግንኙነቶች፡

እናንተ ከወላጆቻችሁ፣ ከእህቶቻችሁ፤ ከወንድሞቻችሁ እና ከሌሎች የቤተሰብ አባላቶቻችሁ ጋራ አዎንታዊ በሆነ አኳኋን መነጋገር አለባችሁ፡፡ በቤተሰብ ውስጥ ወይም በአደባባይ  አወንታዊ ንግግር ማድረግ ሰላምና ስምምነትን ለማስረጽ ይረዳችኋል፡፡

## 4. መተባበርን የሚያበረታቱ እንቅስቃሴዎችን ማዳበር

እርስ በእርስ እንድትደጋገፉ የሚያበረታቱ እንቅስቃሴዎችን ማዘጋጀት ይኖርባችኋል። እንደ እነዚህ ዓይነት እንቅስቃሴዎች በመካከላችሁ ጤናማ ያልሆነ የውድድር ስሜትን በመቀነስ እውነተኛ የእህትማማችነት እና የወንድማማችነት ስሜትን ይፈጥራሉ። እንደ እነዚህ አይነት ተግባራት በቤተሰብ ውስጥ ሰላም እና ስምምነትን ለማስፋፋት እንደ ጥሩ መሣሪያ ሆነው ያገለግላሉ።



ስዕል 3.4 ህጻናት በቤት ዉስጥ ሲተባበሩ

### ፅብረቃዊ መልመጃዎች 3.4

1. በቤተሰብ እና በማሕብረሰቡ ውስጥ ሰላምን ለማስፋፋት የሚረዱ ስልቶችን ዘርዝሩ።
2. በቤት ውስጥ ሰላምን ለማስጠበቅ የወላጆች ሚና ምንድን ነው?

## 3.4. ግጭቶችን/አለመግባባቶችን በሰላም መፍታት

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- ግጭትን/አለመግባባትን መፍታት ማለት ምንድን ነው?

ሰላማዊ የግጭት አፈታት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መካከል ሊከሰት ለሚችል አለመግባባት ሰላማዊ መፍትሄ የመፈለግ መንገድ ነው:: አለመግባባቱ የግል፤ የገንዘብ፣ የፖለቲካ ወይም ሌላ ስሜታዊ ምክንያቶች ሊኖሩት ይችላል:: የትኛውም የጥቃት እና ፀረ-ማህበራዊ ባህሪያት ወይም ተግባራት የትምህርት ቤት መደበኛ አሠራርን ያደናቅፋሉ። እንደዚህ ያሉ ተግባራት በጥቃት ፍርሃት ተማሪዎች እና አስተማሪዎች ትርጉም ባለው የመማር እና የማስተማር ስራቸዉ ላይ እንዳያተኩሩ ሊያደርጋቸው ይችላል:: ስለሆነም እናንተ የግጭት አፈታት ችሎታችሁን በማዳበር የግጭት ምንጮችን እና ውጤታቸውን የመመርመር ሀላፊነት አለባችሁ።

በትምህርት ቤት እና በማህበረሰቡ ውስጥ የትብብር እና የጋራ መከባበር ሀሳቦችን አበረታቱ:: በትብብር እና በስልጠና አማካኝነት በእራሳችሁ ሕይወት ውስጥ የግጭት መንስኤዎችን መረዳት እና አላስፈላጊ ግጭትን ማስወገድ ትችላላችሁ።

**የሚከተለዉን ተረክ/ምንባብ አንብቡ እና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።**

ትንሽ መንደር አለ። የመንደሩ ስም ጥቁር ዉሃ ነው። ትርጉምም ጥቁር ጅረት ነው። የመንደሩ ሰዎች ጉራቲ ብለው ይጠሩት ነበር። ጉራቲ በጣም ንጹህ ውሃ አለው። ብዙ ዓሣዎች እዚያ ይኖራሉ። የመንደሩ ሰዎች ዓሣዎችን ለምግብነት ይጠቀሙ ነበር። አንድ ቀን ተክሉ እና ዳዊት የሚባሉ ሁለት ወጣቶች በጉራቲ ውስጥ ዓሣ ለማጥመድ ለመሄድ ወሰኑ።

ሁለቱም በጅረቱ ዳርቻ ላይ ዓሣ ለማጥመድ በዝግጅት ላይ ሳሉ በድንገት በጅረቱ ውስጥ አንድ ትልቅ ዓሳ አዩ ሁለቱም ወደ ጅረቱ ዘለው በመግባት ዓሳውን ያዙ፡፡ ሁለቱም ትልቁን ዓሳ በእጃቸው ከያዙ በኋላ ለመውሰድ ተስገበገቡ፡፡

ሁለቱም የዓሣው ባለቤት እኔ ነኝ  እኔ ነኝ በማለት እየተከራከሩ ወደ መንደራቸው መጡ፡፡  መላው የመንደሩ ነዋሪም በሁለት በመከፈል ዓሳውን ማን መውሰድ ወይም መያዝ እንዳለበት መከራከር ጀመሩ፡፡ ምሽት ላይ አንድ እንግዳ ወደ መንደሩ መጡ እና የክርክራቸውን ምክንያት ጠየቁ፡፡ የመንደሩ ሰዎችም የግጭቱን መንስኤ አስረዷቸው እንግዳውም በሰሙት ነገር ተገርመዉ እንዲህ ሲሉ መናገር ጀመሩ "ዓሣውን ለሁለት በመክፈል ግማሽ ግማሽ መከፋፈል ወይም ዓሳውን አንድ ላይ  አዘጋጅታችሁ በጋራ አብራችሁ ልትመገቡ ስትችሉ ቀኑን ሙሉ መከራከራችሁ ትርጉም የለሽ ተግባር ነው" ሲሉ ነግሯቸዉ፡፡ ተክሉ እና ዳዊትም እንግዳውን ከሰሙ በኋላ ስህተታቸውን ተገነዘቡ፡፡

ከዛ ጊዜ ጀምሮ ተክሉ እና ዳዊት ጥሩ ጓደኞች ሆኑ፡፡ አንድ ላይ ዓሣ ለማጥመድ ወደ ጥቁር ዉሃ ሲሄዱም የሚያጠምዱትን ዓሳ በእኩል ለመካፈል ወሰኑ፤ መካፈልም ጀመሩ፡፡ ከዚያን ጊዜ በኋላ በመንደሩ መካከል ምንም ዓይነት ክርክር አልተደረገም፡፡

## 3.5 የጽብረቃ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቆዎች መልሱ:

1. ተክሉ እና ዳዊት ምን ወሰኑ?
2. በተክሉ እና በዳዊት መካከል ለተፈጠረው አለመግባባት መንስኤዉ ምን ነበር?
3. የዓሣውን ባለቤትነት በተመለከተ ክርክሩ እንዴት ተጠናቀቀ?
4. የታሪኩ ሥነ ምግባራዊ እሴት ምንድን ነው?

## ሽምግልና

ሽምግልና በህዝቦች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታት ኢትዮጵያውያን ከሚጠቀሙባቸው ባህላዊ ተቋማት ውስጥ አንዱ ነው:: በህዝቦች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን በመፍታት እርቅ እንዲወርድ ያደርጋሉ:: "ሽማግሌ" (የተከበሩ አዛዉንቶች እና እውነተኛ ሰዎች ናቸው) በማህበረሰባቸው ዉስጥ እርቅ እንዲወርድ እና ሰላም እንዲሰፍን ባህላዊ ደንቦቹን በመተግበር ትልቅ ሚና ይጫወታሉ::

ሽማግሌ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች በጥሬው ሲተረጎም አዛውንት ማለት ነው:: ሁኖም በሽምግልና አውድ ውስጥ በሽምግልና ውስጥ የሚሳተፉትን እና በአንድ የተወሰነ ማህበረሰብ ውስጥ የተከበሩትን ወንዶች ይመለከታል እነዚህ ግለሰቦች አለመግባባቶችን እና ግጭቶችን የመፍታት ጥበብ እንዳላቸው ይታመናል:: ሽማግሌዎች በአንድ የተወሰነ ግጭት ውስጥ በተሳተፉ ሁለት አካላት ይመረጣሉ:: የሀገር ሽማግሌዎች በአካባቢያቸው ባህላዊ ደንቦች ላይ በመመርኮዝ ግጭቶችን ለመፍታት ይሞክራሉ:: ይህ ባህላዊ ደንብ በመባል ይታወቃል:: አለመግባባቶች ለትክክለኛ የይገባኛል ጥያቄ በሚቀርቡበት ወቅት በካሳ አማካይነት ይፈታሉ:: በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች እነዚህን ሽማግሌዎች ለማመልከት በተለያዩ ስሞች ይጠራሉ:: ለምሳሌ በአማርኛ የሀገር ሽማግሌ፤ በኦሮሞኛ ጃርሳ ቢያ፤ በጉራጌኛ ኢጆካ፤ በጋሞኛ ድሬጭማ ወ.ዘ.ተ… በማለት ይጠራሉ:: ይህ ልምድ በኢትዮጵያ ማህበረሰቦች ስነ ምግባራዊ እሴቶችን እና መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ የሚተገበር ነው::



ስዕል3.5 ሽማግሌዎች ባህላዊ የእርቅ ስነ-ስርዓት ሲያከናዉኑ

ፅብረቃዊ ተግባር 3.6

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ:

1. በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ግጭቶችን ለመፍታት የሀገር ሽማግሌ ሚና ምንድን ነው?

2. በሰላማዊው የግጭት አፈታት ሂደት ውስጥ የሀገር ሽማግሌ እንዴት ሊመረጡ ይችላሉ?

3. በአከባቢያችሁ ማህበረሰብ ውስጥ በሀገር ሽማግሌነት የተሳተፉ ቢያንስ አምስት ግለሰቦችን ስም ፃፉ፡፡

4. በአከባቢችሁ ውስጥ ግጭቶች እንዴት ይፈታሉ?

5. በትምህርት ቤታችሁ እና በክፍላችሁ ውስጥ ሰላምን ለማስጠበቅ ማድረግ የምትችሏቸውን ተግባራት ዘርዝሩ፡፡

6. የሚከተሉትን ቃሎች ትርጉም ጻፉ፡፡

- የሃገር ሽማግሌ
- ሽምግልና

## 3.5. የሰላም አለመኖር ውጤቶች

የማነቃቂያ ጥያቄ

- የግጭት ውጤት ምንድን ነዉ?

የሰላም አለመኖር በአንድ ሀገር ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ አለው፡፡ በመሣሪያ የታገዙ ግጭቶች ብዙ ችግሮችን ያስከትላሉ፡፡ ለምሳሌ ለመቁሰል እና ለሞት የሚዳረጉ ሰዎች መብዛት፣ የህዝብ መፈናቀል፣ የአስገድዶ መደፈር፣ የሕፃናት ወታደር ምልመላ፤ የበሽታ መስፋፋት፣ የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርታማነት መቀነስ እንዲሁም የንግድ ልውውጥ መቀነስ እና በመሰረተ ልማት ላይ የሚደርስ ጉዳት እንደ ዋነኛ ምሳሌዎች ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም መጥፎ ማህበራዊ ክስተቶች፣ የአካባቢ ጉዳት፣ የወታደራዊ ወጪ መጨመር፣ የምግብ ዋስትና አደጋዎች፣ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት መቀነስ እና የቤተሰብ እና የትምህርት ቤት ብጥብጦች መኖር የጦርነት እና የሰላም አለመኖር ዉጤቶች ናቸው፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

**ሰላም-** በግለሰቦች ወይም በቡድኖች መካከል ከሚደረግ ግጭት እና ጥቃት ነፃ መሆን ማለት ነው::

**ግጭት-** በሁለት ሰዎች ወይም በቡድኖች መካከል ሊኖር የሚችል አለመግባባት ማለት ነዉ፡፡

**መድልዎ-** የሌሎችን መብት ወደ ጎን በማለት ለሆኑ-ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ሆን ተብሎ ፍትሃዊ ባልሆነ መንገድ የሚደረግ የድጋፍ ልምምድ ማለት ነው.፡፡

**እኩልነት-** ሚዛናዊ የሆነ ሂደት ወይም ጥቅሞችን እና እዳዎችን ለማካፈል እድልን ማግኘት መቻል ማለት ነዉ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ሰላም በግለሰቦች ወይም በቡድኖች መካከል የሚደረግ ግጭት አለመኖር እንዲሁም የሰው ልጅ ነጻነትን የሚያሳጡ ፍርሃት እና ብጥብጥ መጥፋት ማለት ነዉ፡፡ ሰላም በአንድ ሀገር ውስጥ ለሁለንተናዊ ልማት እና ሰው ደህንነት አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ሰላም በህብረተሰቡ ውስጥ ሊጠበቅ እና ሊስፋፋ ይችላል፡፡ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መካከል ሊከሰት የሚችል አለመግባባት ለሀገር የሚተርፍ ችግር ይዞ ሊመጣ ይችላል፡፡ ሰላም በማይኖርበት ጊዜ በአንድ ሀገር ውስጥ የሚኖር የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊ እድገት እና ልማት ይቆማል፡፡

## የምዕራፉ ክለሳ መልመጃዎች

**ክፍል አንድ: የሚከተሉት አረፍተ ነገሮችን ትክክል ከሆኑ "እዉነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ።**

1. የሰላም ግንባታ የመንግስት ኃላፊነት ብቻ ነው።
2. በአንድ የተወሰነ ማህበረሰብ ውስጥ ሰላምን የማስጠበቅ የሁሉም ሰው ሀላፊነት አለበት።
3. ሰላምን መጠበቅ ልጆች እና ወጣቶች ትምህርታቸውን ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲማሩ ይረዳል።
4. የሰብአዊ መብቶችን በማክበር እና ታጋሽ ባህሪን በማሳየት በሕብረተሰቡ ውስጥ ሰላምን ማስፈን ይችላል።

**ክፍል ሁለት: ከዚህ በታች ላሉት ጥያቄዎች ከተሰጡ አማራጮች ዉስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።**

1. የሰላም አስፈላጊነት ለማን ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

ሀ. ለግለሰብ　　ሐ. ለማህበረሰብ

ለ. ለቤተሰብ　　መ. ለሁሉም

2. ግጭቶችን መፍታት የማን ሃላፊነት ነው?

ሀ.የሽማግሌዎች　　ሐ የሃይማኖት መሪዎች

ለ. የመንግሥት　　መ. የሁሉም የህብረተሰብ አባላት

3. በቤተሰብ ውስጥ ሰላምን ለማስፈን ከሚከተሉት ስልቶች ውስጥ አንዱ ጥቅም ላይ ይውላል?

ሀ. አላስፈላጊ ውድድር　　ሐ. አሉታዊ ንግግሮች

ለ. መተባበርን አለማበረታታት　　መ. አክብሮት

4.ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የሰላም አለመኖር ውጤት ነው።

ሀ. የኢኮኖሚ እድገት　　ሐ የሕዝብ መፈናቀል

ለ. ማህበራዊ መረጋጋት　　መ. የግብርና ምርታማነትን ማሳደግ

## ክፍል ሶስት፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1. ለግጭት መፍትሄ ለመስጠት የሚያስፈልጉት መሰረታዊ ችሎታዎች እና ባህሪያት ምንድን ናቸዉ?

2. በቤተሰብ ውስጥ ሰላምን ለማስፈን የሚያገለግሉ ስልቶች ምንድን ናቸዉ?

# ምዕራፍ አራት

## ስነ-ምግባር እና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፡-

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የሥነ ምግባርን ጽንሰ-ሀሳብ ትገልፃላችሁ፤
- በማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሥነ-ምግባር አስፈላጊነት ታብራራላችሁ፤
- የመዝናኛ ጊዜን በጥበብ መጠቀምን ታስረዳላችሁ፤
- በማህበረሰብ አገልግሎት ውስጥ አስፈላጊ የሥነ ምግባር መርሆዎችን ዋጋ ትሰጣላችሁ፣
- በማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ዉስጥ የሚደረጉ እና የማይደረጉትን ትለያላችሁ፡፡

### መግቢያ

ሥነ-ምግባር የእሴቶችን ስብስብ በሰዎች ውስጥ ለማስረፅ እና ለማሳደግ ያስችላል፡፡ ከተለያዩ ባህላዊ እና ማህበራዊ ቡድኖች ወይም ሰዎች ጋር በሰላም እንድትገናኙ ያስችላችኋል፡፡ ንቁ እና ኃላፊነት የሚሰማው ዜጋ እንድትሆኑ ያደርጋችኋል፡፡ ሥነ-ምግባር ዘላቂ ጥምረት እና የበለፀገ ማህበረሰብ ለመገንባት ያስችላል፡፡ ልዩነቶችን በማክበር የጋራ መግባባትን እንድትፈጥሩ እና ርህራሄን እንዲኖራችሁ ይረዳችኋል፡፡ የተለያዩ የአለም እይታዎችን በመመርመር በውይይት እና በመግባባት የሕብረተሰቡን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚረዷችሁን የሥነ-ምግባር እርምጃዎችን መውሰድ እንድትችሉ ያስችላችኋል፡፡

የማነቃቂያ ጥያቄዎች

* ከቤተሰብ እና ከትምህርት ቤት ምስጋና ወይም ትችት አጋጥሟችሁ ያውቃል?
* ምስጋናው ምን ስሜት ፈጠረባችሁ?
* በምን ሁኔታዎች ውስጥ ትችቱን ተቀበላችሁ?

## 4.1. የስነ ምግባር ትርጉም

ሥነ-ምግባር በግብረ-ገብ እይታ ትክክል እና ስህተት የሆነውን ጉዳይ እንድንለይ የሚያስችለን መርህ ሆኖ የመልካም ወይም መጥፎ እርምጃዎች ልኬት ነው:: ጥሩ ባህሪዎች በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት ያገኙትን ጥሩ የሥነ-ምግባር እሴቶችን ወይም ደንቦችን ያንፀባርቃሉ:: መጥፎ ባህሪዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላገኙ ናቸው:: ተቀባይነት ያላቸውን ተግባራት ካከናወናችሁ መልካም ሥነ-ምግባር እንዳላችሁ ትቆጠራላችሁ:: ካላደረጋችሁ ደግሞ ሥነ-ምግባር የጎደለው ሰው ተደርጋችሁ ትቆጠራላችሁ::

ፅብረቃዊ ተግባር 4.1

1. የሥነ ምግባርን ትርጉም ግለጹ::
2. በቤት እና በትምህርት ቤት ውስጥ ምን ዓይነት የሥነ-ምግባር ባህሪ ከእናንተ ይጠበቃል?
3. ተማሪዎች በትምህርት ቤት ጥሩ ባህሪ እንዲኖራቸው ለምን እንጠብቃለን?
4. ወላጆቻችሁ በሥነ-ምግባር ባህሪ እናንተን ለማነጽ ያላቸዉን ሚና ጠይቃችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አጋሩ::



ስእል 4.1: ስነ ምግባር በትምርት ውስጥ

የተማሪ ጥሩ ባህሪ መመስረት የሚጀምረው ከቤተሰብ ነው:: በሥነ ምግባር ልጆችን ማሳደግ የወላጆች እና የአሳዳጊዎች ኃላፊነት ነው:: ትምህርት ቤቶችም ተማሪዎችን በጥሩ ሥነ ምግባር በማነፅ በኩል እንደ ወላጆች ተመሳሳይ ኃላፊነት አለባቸዉ:: ትምህርት ቤቶች በስነ ምግባር እሴቶች በሚገባ የታነጹ ዜጎችን ለመፍጠር ተገቢውን ትኩረት መስጠት አለባቸው::

በትምህርት ቤት ውስጥ ተማሪዎች ሥነ-ምግባር ልታሳዩ የምትችሉባቸው በርካታ መንገዶች አሉ የተወሰኑትም እንደሚከተለው ተገልፀዋል-:

- ✓ የክፍላችሁን እና የትምህርት ቤታችሁን ደንቦች ማክበር፤
- ✓ የመማሪያ ክፍሎችን እና የትምህርት ቤታችሁን ንብረት ከጉዳት መጠበቅ፤
- ✓ የትምህርት ቤቱን እና የመማሪያ ክፍሎችን ንፅህና እና ውበት መጠበቅ፤
- ✓ አለመስረቅ፤
- ✓ ሌሎች ሰዎችን አለመሳደብ፤
- ✓ አለመዋሸት፤
- ✓ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ማክበር፤

| በክፍላችን ውስጥ |
|---|
| ቡድን ነን |
| ቀናዎች ነን |
| እንከባበራለን |
| የተሻለ ለመስራት እንሞክራለን |
| ጥሩ ውሳኔ እንወስናል |
| በጎዎች ነን |
| ታማኞች ነን |
| እንደማመጣለን |
| ጠንክረን እንሰራለን |
| እንበረታታለን |
| ሁላችንም አስፈላጊዎች ነን |

ስዕል 4.2: የክፍል ውሰጥ ደንብ ተምሳሌት

**ፅብረቃዊ መልመጃ 4.2**

• የሚከተለውን ሰንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ ገልብጡ እና የተዘረዘሩትን ተግባራት "ስነ-ምግባራዊ" ወይም "ኢ-ስነምግባራዊ" በሚለው ስር ይህን ምልክት "√" አስቀምጡ፡፡

| ተ.ቁ | ተግባር/ባህሪ | ስነ-ምግባራዊ | ኢስነ-ምግባራዊ |
|---|---|---|---|
| 1 | የት/ቤት እና የክፈል ዉስጥ ደንብን ማክበር | | |
| 2 | አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ማገዝ | | |
| 3 | ከሰዎች ጋር መጣላት/መጋጨት | | |
| 4 | ወላጆቻችን እና ታላላቆቻችን ማክበር | | |
| 5 | በአካባቢ ጥበቃ መሳተፍ | | |
| 6 | ሚስጥር መጠበቅ | | |
| 7 | ሀቀኝነት | | |
| 8 | ዉሸት መናገር | | |
| 9 | ማጭበርበር | | |

10. እናንተን በስነ ምግባር በማነፅ በኩል የመምህራን ሚና ምን እንደሆነ እነሱን በመጠየቅ የሚሰጧችሁን መልስ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አጋሩአቸዉ፡፡

## 4.2. በማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የስነ-ምግባር አስፈላጊነት

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

- በማህበራዊ እንቅስቃሴ ዉስጥ ስነ ምግባር አስፈላጊ ነውን?

ሥነ-ምግባር በእያንዳንዱ ማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ አስፈላጊ እሴት ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ሥነ-ምግባር በሁሉም የሕይወት ዘርፎች አስፈላጊ ነው፡፡ ሥነ-ምግባራዊ መሆን እና በቅን ልቦና መስራት ጥሩ ነው፡፡ ጥሩ ዜጋ ለመሆን ሥነ ምግባር ወሳኝ ነው፡፡ሥነ ምግባርን ለመፈጸም ወይም ለመላበስ ከሚያደርጉን ምክንያቶች መካከል ተቀባይነት ማግኘት፤ የተወደደ እና በሌሎች ዘንድ የተከበረ መሆን ናቸዉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሥነ ምግባርን ማጎልበት ህብረተሰቡን በተሻለ ሁኔታ ለመጥቀም፣ ሁሉንም ሰው በእኩልነት ለማገልገል፣ በንግድ ውስጥ ስኬታማ ለመሆን፣ ጭንቀትን ለመቀነስ እና እድገትን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡ ሥነ-ምግባር የጎደለዉ ማለት ስርቆትን፣ ዘረፋን፣ ማጭበርበርን እና ሌሎች ሰዎችን የሚጎዳ ተግባራትን ባህሪዉ ያደረገ ማለት ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ሥነ-ምግባር የጎደለው ሰዉ ዋነኛ ባህሪ ሙስና ነዉ፡፡ ሙስና የሕዝቡን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ህይወት እና የአገሪቱን ልማት በከፍተኛ ሁኔታ ይጎዳል፡፡ የሞራል ብልሹነት ሲኖር ለሙስና ያጋልጣል፡፡

ትምህርታዊ ሐቀኝነት እና ሥነ ምግባራዊ ትክክለኝት ወደ ታላቅ ስኬት ይመራችኋል፡፡ በሥነ-ምግባር ስትታነፁ በማህበራዊ እንቅስቃሴዎቻችሁ ውስጥ በራሳችሁ የምትተማመኑ እና ጽናትን የተላበሳችሁ እንድትሆኑ ይረዳችኋል፡፡ ችግር ላይ ያሉ ሌሎች ሰዎችን መርዳት አስፈላጊ ነው፡፡ የተሻለ ሕይወት መምራት እንድትችሉ የትኞቹ ድርጊቶች ሥነ ምግባራዊ የትኞቹ ድርጊቶች ደግሞ ኢ-ስነምግባራዊ እንደሆኑ መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡



ስዕል 4.3: ልጆች በራሳቸው በማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ዉስጥ ሲሳተፉ እጽዋትን ሲተክሉ እና ሲንከባከቡ፡

## ዕብረቃዊ መልመጃ 4.3

በእያንዳንዱ የማህበራዊ እንቅስቃሴ ዉስጥ የሰዎቹ ባህሪ ጥሩ ወይም መጥፎ ስለመሆኑ አስቡ እና ጥሩ ከሆነ ስነ ምግባራዊ ካልሆነ ደግሞ ኢ-ስነመግባራዊ በሚለዉ ስር ይህንን “√” ምልክት አድርጉ፡፡

| | ስነ-ምግባራዊ | ኢ-ስነምግባራዊ |
|---|---|---|
| 1. ሮዛ ከከድር ጋራ እርሳሷን ትጋራለች፡፡ | ---------- | ------------ |
| 2. አህመድ ለቤተሰቦቹ እና ለጎረቤቶቹ ክብር ይሰጣል፡፡ | ---------- | ------------ |
| 3. ኦባንግ መአዛ የጠፋባትን መጽሀፍ አግኝቶ ሰጣት፡፡ | ---------- | ------------ |
| 4. ሂሩት ከጓደኞቿ ጋር ተራዋን ሳትጠብቅ ትጫዋታለች፡፡ | ---------- | ------------ |
| 5. ኦላና ዳዊት ከብስክሌቱሊወድቅ ሲል ደገፈዉ፡፡ | ---------- | ------------ |
| 6. አይሻ የሺን የቤት ስራዋን ስትሰራ ትረዳታለች፡፡ | --------- | ---------- |

## 4.3. ተገቢነት ያለዉ የእረፍት ጊዜ አጠቃቀም

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

- የእረፍት ጊዜ ምንድን ነው?
- የእረፍት ጊዜያችሁን እንዴት ማሳለፍ አለባችሁ?
- በህይወታችን ዉስጥ የእረፍት ጊዜ በአግባቡ ማሳለፍ ጠቀሜታ አለዉ ብላችሁ ታስባላችሁ?

የእረፍት ጊዜ የህይወት አስፈላጊ አካል ነው። ሁላችሁም የእረፍት ጊዜአችሁን በአግባቡ መጠቀም አለባችሁ። የእረፍት ጊዜ አስፈላጊነት የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል።

- ከዕለት ተዕለት ሥራችን የተለየ ነገር መሥራት፤
- ብዙ ተሰጥኦዎችን ማዳበር፤ እና
- ዘና ባለ ሁኔታ ከቤተሰብ አባላት እና ጓደኞቻችን ጋር መጫወት።

የእረፍት ጊዜን በአግባቡ መጠቀም አዕምሮአችሁን ለማደስ ይረዳችኋል፤ በሕይወታችሁ ውስጥ ሰላም ያመጣል። የእረፍት ጊዜን መጽሐፍትን በማንበብ፣ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በመጫወት፣ በስፖርት እንቅስቃሴዎች በመሳተፍ እና ታሪካዊ ቦታዎችን በመጎብኘት ማሳለፍ በእጅጉ ይጠቅማል።

### የጉንዳን እና የአንበጣ ተረክ

በአንድ በደማቅ የበጋ ቀን አንድ አንበጣ እየዘመረ ሳለ ምግቡን ለመሰብሰብ ጠንክሮ የሚሠራ አንድ ጉንዳን አየ። አንበጣዉ ለጉንዳን “በበጋ ወቅት በጣም ጠንክረህ እንዲህ የምትሰራዉ እና የምትደክመዉ ለምንድን ነው? የበጋ ወራት እኮ የሚመጣዉ እኛ እንድንደሰትበት እና እንድዝናናበት ነዉ። ወደ እኔ ና እና በጋራ እንዘምር እንደሰት” ሲል ጠየቀዉ።

ጉንዳንም ”እኔ ለክረምት የምመገበዉን ምግብ ካሁኑ እሰበስባለሁ፤ ይልቅ አንተም እንደ እኔ እንድታደርግ እመክርሃለሁ” በማለት መለሰለት ፤ አንበጣውም “በአሁኑ ጊዜ ብዙ ምግብ አግኝቻለሁ ለምን ካሁኑ ጀምሬ ስለክረምቱ እጨነቃለሁ?“ በማለት መለሰለት፡፡ ጉንዳን ግን የአንበጣዉን መልስ ችላ ብሎ ስራዉን ቀጠለ፡፡ ከወራት በኋላም ክረምት መጣ፡፡ አንበጣውም የሚበላው ምግብ አጣ፡፡ ርሃቡን ማስታገስ እንዲችል ጉንዳንን ምግብ እንዲሰጠዉ ለመነዉ፡፡ ጉንዳንም “ እኔ ያኔ እንዲያ ስደክም እና ጠንክሬ ስሰራ አንተ ምክሬን ችላ ብለህ ትደሰት ነበር ይሄው ዛሬ ለችግር ተዳረክ” በማለት መልስ ሰጠዉ፡፡ አንበጣዉም ከባለፈው ስህተቱ ተምሮ እራሱን ለማሻሻል ወሰነ፡፡ የዚህ አጭር ትረካ መልእክቱ የእረፍት ጊዜችንን ስናሳልፍ ነጋችንን በማሰብ ከሆነ ዉጤቱ ያማረ ይሆናል ካልሆነ ግን ልክ እንደ አንበጣው ችግር ላይ እንወድቃለን፡፡



ስዕል 4.4 ጉንዳን እና አንበጣ

**ጽብረዊ ተግባር 4.4**

የጉንዳኑን እና የአንበጣዉን ትረካ አንብባችሁታል? ጎበዞች!

1. ካነበባችሁት ተረክ ምን ተማራችሁ?
2. በአጭር ታሪክ ዉስጥ ለእናንተ በሳል ጉንዳን ወይስ አንበጣ? ______________ ከሆነስ ለምን?

የቡድን ውይይት መልመጃ

1. ስንፍና ምንን ያስከትላል?
2. በስራፈትነት እና በእረፍት ጊዜ ስላለው ልዩነት ተወያዩ።

## 4.4. በማህበረሰቡ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚደረጉ እና የማይደረጉ ተግባራት

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

- በማህበረሰባዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚደረጉ እና የማይደረጉ ተግባራትን የመለየት ጠቀሜታ ምንድን ነዉ?
- በትምህርት ቤታችሁ እና በመኖሪያ አካባቢያችሁ የሚተገበሩ/የሚደረጉ እና የማይተገበሩ የተወሰኑ ተግባራትን ጥቀሱ?

በማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ በማድረግ እና ባለማድረግ የሚገለጹ ብዙ የሥነ-ምግባር ጉዳዮች አሉ። በመልካምነት የሚገለጹ የሥነ-ምግባር እሴቶች ወይም ተግባሮች በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያገኙ ድርጊቶች ሲሆኑ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላገኙ ድርጊቶችን ደግሞ ባለማድረግ የሚገለጹ ተግባራት ናቸዉ።

በማድረግ የሚገለፁ የስነምግር እሴቶች ምሳሌዎች፡-

- ✓ እናት አባቶቻችሁ ሲመክሯችሁ መስማት፤
- ✓ በአቅማችሁ ልክ ቤተሰቦቻችሁን መርዳት፤
- ✓ ከእኩያዎቻችሁ ጋር ተራችሁን ጠብቃችሁ መጫወት፤
- ✓ ለታላላቆቻችሁ አክብሮት መስጠት፤
- ✓ የግል ንጽህናችሁን መጠበቅ፤
- ✓ በአግባቡ የቤት ስራችሁን መስራት፤
- ✓ ጠንክሮ ማጥናት፤
- ✓ መምህራንን ማክበር፤
- ✓ መልካም ወንድማማችነትን፤ ጉርብትናን እና ጓደኝነትን ማሳደግ፤
- ✓ ማህበረሰባችሁን እና ሃገራችሁን መዉደድ፤

ባለማድረግ የሚገለጹ  የስነ ምግባር  እሴት ምሳሌዎች:

- በፈተና ወቅትም ሆነ በሌላ ጊዜ አለማጭበርበር፤
- የሰውን ንብረት አለመስረቅ፤
- የመማሪያ ቁሶችን አለማዉደም/አለማበላሸት፤
- ከትምህርት ቤት አለመቅረት፤
- አለማርፈድ፤ ወዘተ

ፅብረቃዊ  መልመጃ 4.5

ቀጥሎ ያለዉን መልመጃ ወደ ደብተራችሁ ጻፉ። ከቤተሰቦቻችሁ ጋር በመወያየትም ባዶ ቦታዉን ተጨማሪ በማድረግ የሚገለጹ  እና  የማይገለጹ ተግባራትን በመጻፍ ሙሉ። ከዛም በምሳሌው መሰረት የሚደረጉ ወይም የማይደረጉ በሚለው ስር ምልክት አድርጉበት።

| ተ.ቁ | ተግባራት | የሚደረጉ | የማይደረጉ |
|---|---|---|---|
| 1 | መምህራንን፤ታላላቆችንና ወላጆችን ማክበር | | |
| 2 | ማረፊድ | | |
| 3 | | | |
| 4 | | | |
| 5 | | | |
| 6 | | | |
| 7 | | | |
| 8 | | | |
| 9 | | | |

## በቤት ውስጥ የሚደረጉ እና የማይደረጉ ተግባራት

ምግብ ከመብላታችሁ በፊት እና በኋላ እጃችሁን ታጠቡ:: ቀስ ብላችሁ ተመገቡ እና ምግባችሁንም በደንብ አኝኩ:: ለረጅም ጊዜ ያለጥንቃቄ የተቀመጠ ምግብን አትመገቡ:: የኤሌክትሪክ ገመዶችን፣ የተላጡ ሽቦዎችን፣ ወይም የኤሌክትሪክ ማሽኖችን በጭራሽ አትንኩ ወይም አትጫወቱ:: በቤት ውስጥ ብዙ ጠቃሚ የሆኑ ቁሶች አሉ:: ነገር ግን እንደ መቀስ፤ ቢላዋ፤ አምፖሎች፤ መርፌዎች፣ ወዘተ የመሳሰሉትን ቁሶች ስላታም ስለሆኑ በጥንቃቄ ልንጠቀምባቸው ይገባል:: እናንተ በጭራሽ እነሱን መንካት የለባችሁም::



የኤሌክትሪክ ማሽን



የተላጠ ኤሌክትሪክ ገመድ



ምላጭ ቢላዋ አምፖል መርፌ

ስእል 4.5 ስለታማ ቁሶች

### በመኖሪያ አካባቢያችን የሚደረጉ እና ያማይደረጉ ድርጊቶች

ሕጎችን ማክበር፣ ጠቃሚ ምክሮችን ማዳመጥ እና ሥነ ምግባራዊ መሆን ጤናችንን ይጠብቅልናል:: የማታውቁትን ፍራፍሬ ወይም የዕፅዋት ፍሬዎች አትብሉ:: አንዳንዶቹ መርዝ ሊሆኑ እና ሊያሳምሟችሁ ይችላሉ:: እንስሳትን በፍፁም መጫወቻ አታድርጓቸው ወይም አታንገላቱዋቸው:: አትዋኙ፤ ብቻችሁን አትዋኙ፤ በውሃው አትጫወቱ፤ በአንድ ሰው ጆሮ ውስጥ በጭራሽ አትጮሁ ወይም በዶቃዎች ወይም ሹል ነገሮች ጆሮችሁን አትጎርጉሩ ወይም ጆሮአችሁ ውስጥ አታስገቡ::

### በመንገድ ላይ የሚደረጉ እና የማይደረጉ ድርጊቶች

ሁል ጊዜ ዓይኖቻችሁን እና ጆሮዎቻችሁን ክፍት አድርጉ:: የሚመጡ ተሽከርካሪዎች ድምፅ አዳምጡ፤ በመንገድ ላይ በጭራሽ አትጫወቱ፤ በመንገድ ላይ ስትራመዱ የእግረኛ መንገድን ተጠቀሙ፤ መንገዶችን ስታቋርጡ የተፈቀዱ የማቋረጫ መንገዶችን (ዜብራ) ብቻ ተጠቀሙ:: መንገዱን ከማለፋችሁ በፊት በሁሉም አቅጣጫዎች በጥንቃቄ ተመልከቱ::

### በትምህርት ቤት ውስጥ የሚደረጉ እና የማይደረጉ ድርጊቶች

ጥሩ ባህዎች ካለን ከብዙ አደጋዎች ይጠብቁናል:: መጥፎ ባህሪ ደግሞ ለብዙ አደጋዎች ይዳርጉናል:: ለዚህም ነው በትምህርት ቤት ውስጥ የትምህርት ቤት ህጎች እና ደንቦቹ ሊኖሩ የቻሉት:: እነኝህን ህጎች ስናከብር እራሳችንም ሆነ ሌሎችን አንጎዳም:: ሰዓት አክባሪ ሁኑ:: ሁልጊዜም የሚቻላችሁን ጥረት አድርጉ:: መልካም ቃላትን እና ድርጊቶችን ተጠቀሙ:: የትምህርት ቤታችሁን የአለባበስ ደንብ ተከተሉ:: ሁልጊዜ የቤት ስራ እና ሌሎች የሚሰጡ ተግባራትን በሚገባ ስሩ:: የእጆቻችሁን፣ የእግሮቻችሁን እና የዕቃዎቻችሁን ንጽህና ጠብቁ:: በጠረጴዛዎች ላይ አትውጡ:: ለክፍል ጓደኞቻችሁ እንክብካቤ አድርጉ:: በክፍሉ ውስጥ በምንም ነገር አትጣሉ::.ተራችሁን ጠብቃችሁ ተጫወቱ በምትጫወትበት ጊዜም ታጋሽ ሁኑ::

## የፅብረቃ ተግባራት 4.6

**ክፍል አንድ፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ዓረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እዉነት" ትክክል ካልሆነ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልስ ስጡ።**

1. ደንቦችን እና ህጎችን ስታከብሩ እናንተን ከአደጋ ይጠብቃችኋል።
2. በስነ ምግባር በመታነፅ እና በመመራት አደጋዎችን ማስወገድ ይቻላል።
3. ሁሌም ህጎችን እና መመሪያዎችን መከተል አለብን።
4. የሚፈሩ እንስሳት አደገኛ ሊሆኑ ይችላሉ።
5. ብቻችንን መዋኘት አደገኛ ሊሆን ይችላል።
6. ሕጎችን ማክበር፣ ጠቃሚ ምክሮችን ማዳመጥ እና ሥነ ምግባራዊ መሆን ጤናችንን ይጠብቃል።

**ክፍል ሁለት. ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ይምረጡ።**

1. ---------- አትጫወት።
   - ሀ. በስለታም ነገሮች
   - ለ. ከጓደኞችህ ጋር
   - ሐ. በአስተማማኝ መጫወቻዎች
   - መ. በኳስ
2. የትኛው መንገድ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው።
   - ሀ. የእግረኛ መንገድ
   - ለ. ሥራ የሚበዛበት መንገድ
   - ሐ. ጠመዝማዛ መስመሮች
   - መ. የመሀል መንገድ
3. መንገድን በደህንነት ለመሻገር.........መጠቀም አለብን።
   - ሀ. በየትኛውም መንገድ
   - ለ. በተፈቀደ የማቋረጫ (ዜብራ)
   - ሐ. በመንገዶች ላይ በመጫወት
   - መ. በመንገድ ላይ መሮጥ
4. በምትጫወቱበት ጊዜ............አትሁኑ።
   - ሀ. አስቸጋሪ
   - ለ. ታጋሽ
   - ሐ. ደግ
   - መ. ፍትሀዊ

### የሚከተለውን ተረት አንብቡ።

## ለጥሩ ሥነ-ምግባር በሚደረጉ ተግባራት ላይ ማተኮር ያለው ጠቀሜታ

ሳምሶን የ4ኛ ክፍል ተማሪ ነው። በቤተሰቡ፣ በጎረቤቶቹ እና በክፍል ጓደኞቹ ዘንድ በጨዋነቱ ይታወቃል። ሳምሶን በባህሪው ብቻ ሳይሆን በጥሩ የትምህርት ውጤቱም የተከበረ ነው። ጎበዝ ተማሪ ሲሆን በጓደኞቹ እና በአስተማሪዎቹ ዘንድ ተወዳጅ ነው። የትምህርት ቤቱን ህግና መመሪያ ባለመጣስ ይታወቃል። ብዙ ሰዎች እሱን "ብልህ ልጅ" ብለው ይጠሩታል። ከትምህርት ቤት በኋላ በተለያዩ ክበባት ውስጥ ይሳተፋል። በተለይም በግብረ-ገብ ክበብ ውስጥ ያለው ሚና በጣም ከፍተኛ ነው። በእሱ ንቁ ተሳትፎ ምክንያት፣ በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ሁለት ጊዜ ተሸልሟል። ሳምሶን በማህበረሰቡ ውስጥ በመልካም ባህሪው እና በትምህርቱ ከፍተኛ ውጤት ምክንያት ለሌሎች ተማሪዎች ተምሳሌት ተማሪ ነው ተብሎ ይታመናል።

### ፅብረቃዊ ተግባራት 4.7

ከላይ ያለውን ተረክ አነበባችሁት? ጎበዞች!

**በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡-**

1. መልካም ባህሪን መላበስ ጠቀሜታው ምንድን ነው?
2. ሳምሶን መልካም ባህሪውን እና ትምህርታዊ ብቃቱን ያዳበረው እንዴት ነው?
3. ከላይ ካለው ተረክ ምን ተማራችሁ?

## ፅብረቃዊ መልመጃዎች 4.8

ጥሩ ስነ ምግባር የተላበሱ ምርጫዎችን ማድረግ

በእያንዳንዱ ሁኔታ ከሥነ ምግባር አኳያ ጥበበኞች ናቸው ብላችሁ ከምታምኑት አማራጭ(ዎች) ቀጥሎ ይህንን ምልክት ያድርጉ (“√”)።

1. እናትህ/ሽ ክፍልህን/ሽን እንድታጸዳ/ጂ ትናገራለች። አንተ/ቺ ደግሞ ታናሽ እህትህ/ሽ እንድታፀዳው/እንዲያፀደው ትተወዋለህ/ሽ ወይስ

——— ራስህ/ሽ ታጸዳለህ/ጃለሽ።

——— ከተጫወትክ/ሽ በኋላ ለማጽዳት ቃል ትገባለህ/ሽ።

——— ያጸዳህው አስመስለህ ትተወዋለህ።

2. የሆኑ ሰዎች የሌላ ልጅን መጽሐፍ እና ቦርሳ ወስደው ሲሮጡ ብታዩ ምን ታደርጋላችሁ?

——— ምንም አላደርግም።

——— ልጆቹን ተከትዬ በመሮጥ እንዲመልሱ ለማድረግ እሞክራለሁ።

---------ለመምህራኑ ወይም ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር እናገራለሁ።

3. በመጫወቻ ቦታ ላይ የኪስ ቦርሳ ብታገኙ እናንተ ብትሆኑ

——— ቦርሳውን ወደ ቤት ትወስዳላችሁ፤

——— የኪስ ቦርሳውን ለትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር ወስደህ ታስረክባላችሁ፤

——— ለጓደኞችህ ትሰጣላችሁ፤

## የሚቀጥለውን ጽሁፍ አንብቡና ተከታዩን ጥያቄ መልሱ

### የኔ የጥርስ ቡሩሽ

ስሜ ሙሴ ሲሆን የ4ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ። ይህ አረንጓዴ የጥርስ ብሩሽ የኔ ነው። በየቀኑ በቀን ሦስት ጊዜ ማለትም ጠዋት ላይ እኩለ ቀን ላይ እና ከመተኛቴ በፊት ጥርሴን ለማጽዳት እጠቀምበታለሁ። እናቴ ጥርሴን እንዴት መፋቅ እንዳለብኝ አስተምራኛለች። የጥርስ መፋቂያዬን እንኳ ለሌሎች ሰዎች ለቤተሰቤ አባላትም ቢሆን እንዳልሰጥ አስተምራኛለች። ንጹህ እና ጤናማ ጥርስ እና ድድ እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ። እናቴን አመሰግናለሁ።



ስዕል 4.6 ልጆች ጥርሳቸውን በጥርስ ብሩሽ ሲያፀዱ

### ፅብረቃዊ መልመጃዎች 4.9

1. ሙሴ የጥርስ ብሩሽ ለምን ይጠቀምበታል?
2. ሙሴ የጥርስ ብሩሹን ከሌሎች ጋር ይጋራል?
3. የጥርስ ብሩሹን ለሌሎች ለምን አያጋራም?

## 4.1.1 የመንገድ ትራፊክ እና ደህንነት

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

* መንገድ ለማቋረጥ ደህንነታቸዉ የተጠበቁ ቦታዎችን ግለጹ፤
* መንገድ ለማቋረጥ ደህንነታቸው ያልተጠበቁ ቦታዎችን ግለጹ፤
* ልጆች በመንገድ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ለምን እንደፈለጉ አብራሩ፤




ስዕል 4.7 የመንገድ ትራፊክ እና ደህንነት የመንገድ ትራፊክ እና ደህንነት

የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ግብ በተሽከርካሪ ብልሽቶች ምክንያት የሚፈጠረውን ጉዳት (ሞት፣ የአካል እና የንብረት ጉዳትን) ለመቀነስ ነው:: ይህንን ግብ ለማሳካት ሊተገበሩ የሚገቡ አንዳንድ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ህጎች የሚከተሉት ናቸው-:

- ✓ የመንገዱን ሁለቱንም አቅጣጫዎች ከተመለከትን በኋላ መንገዱን ማቋረጥ::
- ✓ በመንገድ ላይ ማተኮር::
- ✓ በጎዳናዎች ላይ አለመሮጥ::
- ✓ መንገዱን በምታቋርጡበት ጊዜ ትኩረታችሁን መንገዱ ላይ ማድረግ::
- ✓ መንገዱን ስታቋርጡ አለመወያየት / አለማውራት ::
- ✓ በእግር በምትጓዙበት ጊዜ የእግረኛ መንገዶችን ብቻ መጠቀም::ለመራመድ የምትጠቀሙበት ብቸኛው መንገድ የእግረኛ መንገድ ነው::

- ✓ በተፈቀዱ የማቋረጫ መንገዶች (zebra) ላይ ብቻ መንገዱን ማቋረጥ:: በሌላ ቦታ ላይ ፈጽሞ መንገዱን ማቋረጥ የለባችሁም::
- ✓ በድፍረት ሮጣችሁ አትግቡ፤ በቆሙ መኪናዎች መካከል በጭራሽ ማቋረጥ የለባችሁም::
- ✓ በመኪና ውስጥ ስትሆኑ ቀበቶ ማሰር እና ከተሳፈራችሁበት መኪና ውጭ የትኛውንም የሰውነት ክፍላችሁን በጭራሽ ማስወጣት የለባችሁም::
- ✓ ሞተር ብስኪሌት በምትነዱበት ጊዜ የብስክሌቱን የደህንነት መጠበቂያ አድርጉ::
- ✓ ወደ መኪና በምትሳፈሩበት እና በምትወርዱበት ጊዜ እንዲሁም በመንገድ ላይ በምትራመዱበት ጊዜ ታጋሽ ሁኑ እንዲሁም ተራችሁን ጠብቁ::

## ውስን ጥናት

ኤደን ወደ ትምህርት ቤት በጥዋት ትሄደለች::

የተረቱን ርዕስ በመመልከት ተረቱ ስለ ምን ሊሆን እንደሚችል ገምቱ::

ሰኞ ጠዋት ኤደን ከእናቷ ጋር ወደ ትምህርት ቤት ስትሄድ በእናቷ እጅ ተይዛ በእግረኛ መንገድ ተጓዙ:: የኤደን እናት ኤደን ወደ ትምህርት ቤት ስትሄድ ደህንነቱ የተጠበቀ መንገድ እንድትጠቀም እና መንገዱን ስታቋርጥም የተፈቀደ የማቋረጫ መንገድ ብቻ እንድትጠቀም ገልጻላታለች:: እናቷ ለኤደን ወደ ትምህርት ቤት የሚወስደው የእግረኛ መንገድ ያን ያህል በትራፊክ የተጨናነቀ እንዳልሆነ እና ሁለት የማቋረጫ መንገዶችን ብቻ እንዳሉም አብራራችላት:: ስለሆነም መንገዱ በጣም ደህንነቱ የተጠበቀ ነው ስትልም አስረዳቻት:: ኤደን ከመንገዱ ጫፍ ሲደርሱ "መንገዱን ከማቋረጣችን በፊት ምን ማድረግ አንዳለብኝ ንገሪኝ" ስትል እናቷን ጠየቀች እናቷም "ደህና ከመንገዱ ጫፍ ላይ እንቆማለን ተሽከርካሪ እንዳለ እና እንደሌለ እናያለን ወደ እኛ የሚመጣ የመኪና ድምጽ እናዳለ እና እንደሌለ እንሰማለን እና ተሽከርካሪ ከሌለ ለማቋረጥ ጥሩ ነው ብለን በማሰብ ተረጋግተን እንሻገራለን::"

በማለት በተግባር ጭምር አሳየቻት፡፡ ኤደንም በደንብ ገብቶኛል በማለት መለሰች፡፡ ኤደን ትምህርት ቤት እንደደረሰች ከእናቷ ጋር ያሳለፈችዉ ጊዜ ጥሩ እንደሆነ ገልጻ ደህና ሁኚ እማዬ በማለት ሄደች፡፡

ማክሰኞ ጠዋት ኤደን ከእናቷ ጋር ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ አውቶቡስ ያዙ፡፡ በመስኮቱ አጠገብ ተቀምጣ ሁሉንም መኪኖች ተመለከተች፡፡ አውቶቡሱ ለመንቀሳቀስ ጊዜው ሲደርስ ጡሩንባውን (ክላክስ) ነፋው፡፡ ኤደን እናቷን "ከአውቶቡስ ስንወርድ ምን ማድርግ እንዳለብኝ ንገሪኝ ስትል ጠየቀቻት፡፡ እናቷም ከአውቶቡሱ በኋላ በር ስንወጣ አውቶቡሱ ቦታ እስኪለቅ ድረስ ከአውቶቡሱ በስተጀርባ ያለውን መንገድ ሳናቋርጥ እንጠብቃለን፡፡ ከዚያ አውቶብሱ ሲሄድ መንገዱን ለማቋረጥ መንገዱ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ከተሽከርካሪ ነጻ መሆኑን አረጋግጠን እንሻገራለን " በማለት ነገረቻት፡፡

የተነገረችዉን በተግባር ከሞከረች በኋላ ኤደን በደንብ ተከናውኗል! አለች፡፡ ኤደን በመቀጠልም በአውቶቡስ ላይ ሆኜ ከፍ ያሉ ነገሮች ማየት ደስ ይለኛል አለች፡፡ ኤደን ወደ ትምህርት ቤት እንደደረሰችም እማዬ ያሳለፍነው ጊዜ አስደሳች ነበር ደህና ሁኚ እማዬ ብላ ወደ ትምህርት ቤቷ ገባች፡፡



ስዕል 4.8: ኤደን ከእናቷ ጋር ወደ ትምህርት ቤት ስትሄድ

ፅብረቃዊ መልመጃ 4.10

ከላይ በተሰጣችሁ ተረክ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎችን መልሱ

1. መንገድ ከመሻገራችሁ በፊት ምን ታደርጋላችሁ?
2. ከአውቶብስ ስትወጡ ምን ታደርጋላችሁ?
3. ወደ ትምህርት ቤት ስትሄዱ ኤደን በእናቷ እጅ ለምን እንደተያዘች አብራሩ::

## 4.5. የስነ ምግባር መርሆዎች በማህበረሰብ አገልግሎት ውስጥ

የማነቃቂያ ጥያቄዎች

- ለማህበረሰብ አገልግሎቶች ምን ዓይነት የሥነ-ምግባር መርሆዎች ሊተገበሩ ይችላሉ?
- በማህበረሰብ አገልግሎት ውስጥ የሥነ-ምግባር መርሆዎች ጥቅም ምን ምን ናቸው?



ስዕል 4.9: ችግረኞችን መርዳት እና መደገፍ

የሥነ-ምግባር መርሆዎች በማህበረሰብ አገልግሎቶች ውስጥ በጣም አስፈላጊ ናቸው:: የሥነ ምግባር መርሆዎች የጎደላቸው የማህበረሰብ አገልግሎቶች ተልእኮዎቻቸውን ማሳካት አይችሉም:: ትክክለኛ የማህበረሰብ አገልግሎት ተሞክሮ ደግ ለመሆን ሊረዳችሁ ይችላል: ትርጉም ላላቸው ግንኙነቶች መጀመሪያ ሊሆን ይችላል:: እንደ መሰረታዊ የሰብአዊ መብቶች መከባበር፣ ፍትሃዊነት ያሉ የሥነምግባር ጉዳዮች ምስጢራዊነት፣ ርህራሄ፣ ስምምነት፣ ቁርጠኝነት እና ብቃት አስፈላጊ ናቸው:: እንደ ልብስ መስጠት(መርዳት)፣ አከባቢያችሁን ማጽዳት፣ አካባቢያችሁን መገንባት ወይም ማስዋብ በመሳሰሉት ማህበራዊ አገልግሎቶች ውስጥ መሳተፍ ትችላላችሁ::

የመማሪያ ክፍላችሁን ማጽዳት፣ አንድ ሰዉ ከትምህርት ቤት በኋላ ወይም ከመደበኛ ትምህርት ውጭ በማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲሳተፍ ማበረታታት በተጨማሪም ፣ እናንተ ያነበባችሁትን መጽሐፍ መስጠት ፣ የትምህርት ቤት ቁሳቁሶችን ከጉዳት መከላከል ፣ ወዘተ... በስነምግባር መከናወን የሚችሉ የማህበረሰብ አገልግሎቶች ናቸው::

እኔ ----------- ለእራሴ በትምህርት ቤት ቆይታዬ ምን መሆን እንደምፈልግ ለማሳየት ቃል እገባለሁ:: በትምህርት ቤት ቆይታዬ ማወቅ ያለብኝን ነገሮች በመማር ፣ እንደ እኔ ላሉት ልጆች ዓለም የተሻለ ቦታ እንድትሆን ለማድረግ ቃል እገባለሁ:: ህልሜን ለማሳካት፣ በሕይወት ለመቆየት እና እኔ መሆን የምችለውን ሁሉ ለመሆን ቃል እገባለሁ:: እኔ እንደምችል አውቃለሁ ::

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ሥነ-ምግባር የመልካም እና መጥፎ ድርጊቶች ወይም ባህሪዎች ልኬት ነው::መከበር ያለባቸው በርካታ የሥነ-ምግባር ጉዳዮች አሉ:: እናንተ የሚደረጉ እና የማይደረጉ የስነ-ምግባር ባህሪያትን መለየት አለባችሁ::ህጎችን ማክበር፣ ጠቃሚ ምክር ማዳመጥ እና በሥነ ምግባር መታነጽ ጤናማ እንድትሆኑ ያደርጋችኋል:: በቤት ውስጥ፣ በጎዳናዎች እና በትምህርት ቤት ጥሩ የስነ ምግባር ባህሪ መላበስ ከብዙ አደጋዎች ይጠብቃችኋል:: መጥፎ ባህሪ ግን ለብዙ አደጋዎች ይዳርገናል:: ለዚህም ነው ለትምህርት ቤት እና ለማህበረሰቡ ህጎች እና ደንቦች እራሳችሁን እንድታስገዙ የሚጠበቀው::

### ቁልፍ ቃላት

**ስነ ምግባር-** አንዳንድ ባህሪያትን እንደ ጥሩ እና ሌሎችን እንደ መጥፎ አድርጎ የሚመደብ የሰዎች ባህሪ ደረጃ ነው::

**የሚደረጉ:-** እንዲከናወኑ የተፈቀዱ እንቅስቃሴዎች::

**የማይደረጉ-** እንዲከናወኑ ያልተፈቀዱ እንቅስቃሴዎች ማለት ነው.

**ግብረ-ገብ-** ትክክለኛውን ነገር የማድረግ ፅንሰ-ሀሳብ ነው.

**ትክክል መሆን** - በጥሩ ወይም በተገቢው መሠረት አንድን ነገር መፈጸም መቻል ነው:;

**ስህተት-** በሥነ ምግባር እይታ ትክክል ወይም ጥሩ ያልሆነ::

## የምዕራፉ ክለሳ መልመጃዎች

**ክፍል አንድ፡-.የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እዉነት" ትክክል ካልሆነ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ።**

1. ሥነ ምግባር ሰዎች አብረው ሲኖሩ የሚጠቀሙበት አስፈላጊ መሣሪያ ነው።
2. ፈተና መኮረጅ መደረግ ያለበት ባህሪ ምሳሌ ነው:;
3. ምስጢር መያዝ የታማኝነት እና ጥሩ የሥነ-ምግባር ባህርይ ልኬት ነው።
4. የሥነ-ምግባር መርሆዎች በማህበረሰብ አገልግሎቶች ውስጥ በጣም አስፈላጊ ናቸው።

**ክፍል ሁለት: በ "ለ" ስር የተዘረዘሩትን ቃላት ወይም ሀረጎች በ "ሀ" ስር ከተዘረዘሩት ትክክለኛ ፍቺ ጋር አዛምዱ**

| ምድብ 'ሀ' | ምድብ'ለ' |
|---|---|
| 1. መነገር የሌለበት ጉዳይ | (ሀ) መደረግ ያለበት |
| 2. የተፈቀዱ ድርጊቶች | (ለ) መደረግ የሌለበት |
| 3. አግባብነት በሌለውሁኔታ ለመጫወት መሞከር | (ሐ) ሚስጥር |
| 4. ተቀባይነት ያላቸው እና የሌላቸው ባህሪያት ልኬት | (መ) ስነ መግባር |
| 5. ለህጻናት የስነ ምግባር ግንባታ የሚጀመርበት ቦታ | (ሠ) ቤተሰብ |

**ክፍል ሦስት፡ ከዚህ በታች ለተሰጡ ለእያንዳንዱ ጥያቄዎች ከተሰጡ አማራጮች ውስጥትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ የትኛው ሥነ-ምግባር የጎደለው ባህሪ ምሳሌ ነው?

   ሀ. የትምህርት ቤት ህጎችን እና መመሪያዎችን ማክበር፡፡

   ለ. የመማሪያ ክፍሉችን ንፁህ ማድረግ፡፡

   ሐ. የሌሎች ተማሪዎችን ንብረት አለመውሰድ፡፡

   መ. ከሌሎች ጋር መደባደብ፡፡

2. በጓደኞች መካከል ቃል ኪዳንን ሊይዝ የሚችል ስምምነት............ በመባል ይታወቃል

   ሀ. የቤተሰብ ምስጢር　　　ለ. የጓደኛ ምስጢር

   ሐ. ብሔራዊ ሚስጥር　　　መ. የትምህርት ቤት ምስጢር

3. በእረፍት ጊዜዬ ፣ እኔ..............................

   ሀ.አነቃቂ መጽሐፍትን አነባለሁ፡፡

   ለ. ስለ ማንበብ አላስብም፡፡

   ሐ. በአደገኛ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እሳተፋለሁ፡፡

   መ. ከእንስሳት ጋር እጫወታለሁ፡፡

4. በስራዬ ቤተሰቦቼ------------እሞክራለሁ.

   ሀ.እንዲረኩ　ለ. እንዳይረኩ　ሐ. ተስፋ እንዲቆርጡ　መ. ለማናደድ

5. ከመልካም ሰው----------እንማራለን.

   ሀ. ጥሩ ሥራ　　　ሐ. ሥነ ምግባር የጎደለው ባህሪ

   ለ. መጥፎ ሥራ　　　መ. የተሳሳቱ እርምጃዎችን

6.የጥሩ ሰው ተጽዕኖ.......ነው

   ሀ.አዎንታዊ　　　ሐ. ምንም

   ለ. አሉታዊ　　　መ. ጉዳት

ክፍል አራት፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎችን በደብተሩችሁ ገልብጡ እና ባዶ ቦታዎችን በትክክለኛው መልስ ሙሉ።

1. በአካባቢው ማህበረሰብ ተቀባይነት ያለው ባህሪ/ተግባር ምን በመባል ይታወቃል?------------

(ጥሩ ባህሪ / መጥፎ ባህሪ)

2. ጥሩ ባህሪዎች የሚጀምሩት ከ------------------

(ትምህርት ቤት/ቤተሰብ ) ነው።

3. ከተማሪዎች የሚጠበቁትን ቢያንስ ሦስት የስነምግባር እሴቶችን ዘርዝሩ.

# ምዕራፍ አምስት

## የመቻቻል ባህል

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፡-**

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የመቻቻልን ባህል ትገልጻላችሁ፡፡
- የመቻቻል ባህል አይነቶችን ትለያላችሁ፡፡
- የመቻቻልን ባህል አስፈላጊነት ትገልጻላችሁ፡፡
- የመቻቻል ልማዶችን ታሳያላችሁ፡፡
- የመቻቻል ባህል ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶችን ትዘረዝራላችሁ፡፡

### መግቢያ

ቀደም ባሉት የትምህርት ደረጃዎች ላይ ከቤተሰቦቻችሁ፣ ከትምህርት ቤታችሁ እና ከማሕበረሰብ ደንቦች ጋር በተያያዘ ሌሎችን ማክበር የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ ተምራችኋል፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ስለ መቻቻል ባህል ከተለያየ የማህበራዊ ህይወት እይታ ትማራላችሁ፡፡ በተጨማሪም ምዕራፉ የመቻቻል ባህል፣ የመቻቻል ባህል አስፈላጊነት፣ እና የመቻቻል ባህል ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮችን ከግምት ውስጥ አስገብቷል፡፡

## 5.1 የመቻቻል ባህል ጽንሰ-ሐሳብ

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

- መቻቻል ምን እንደሆነ ግለጹ?
- በማህበረሰቡ ውስጥ የመቻቻል አስፈላጊነት ምንድን ነው?

የመቻቻል ባሕል የሚያመለክተው የመተሳሰብ እና የመቻቻልን ሂደት ነው:: እንደዚሁም ፍትሃዊ እና ዓላማ ያለው፣ የሌሎችን ግለሰቦች ሃሳቦች፣ አስተያየቶች እና ልምዶች መቀበል ማለት ነው:: ለምሳሌ:- ኢትዮጵያ በመቻቻል እሴቶች የምትታወቅና ከሰማንያ በላይ ብሔሮች እና ብሔረሰቦችን አቻችላ የምትኖር ሀገር ነች:: በርካታ ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎችና በልዩ ልዩ ባህላዊ ቡድኖች መካከል ተጋርተዋል::

የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱ አለመግባባቶችን የመፍታት ባሕል እንዲሁም የይቅር ባይነት ባህልን አዳብሯል:: መቻቻል ትኩረቱ ፍቅርና ይቅር ባይነት ነው:: ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች በልዩ ልዩ ባህላዊ ቡድኖች መካከል ተጋርተዋል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱ የሆነ አለመግባባቶችን የሚፈታበት እንዲሁም የይቅር ባይነት ባህልን አዳብሯል:: መቻቻል ትኩረቱ ፍቅር እና ይቅር ባይነትን ማምጣት ነው::

**ፅብረቃዊ ተግባራት 5.1**

1. በአራት ቡድን ሆናችሁ ከላይ ከተጠቀሰው አንቀፅ ምን እንደተማራችሁ ተወያዩ?
2. “የመቻቻል ባህል” ማለት ምን ማለት ነው?

## 5.2. የመቻቻል ባህል ዋና ዋና መገለጫዎች

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- የመቻቻል ዋና ዋና መገለጫዎች ምንድን ናቸው?

መቻቻል ሰዎች በሰላም አብረው እንዲኖሩ የሚረዳ ጠቃሚ ፅንሰ-ሀሳብ ነው፡፡ መቻቻል ሁሉም ግለሰቦች በማኅበራዊ ግንኙነታቸው ውስጥ የተለያየ አመለካከት እና እምነትን ተቀብሎ የመኖር ጥበብ ነው፡፡ መቻቻል ማለት የሌሎችን ሰዎች አመለካከትና ምርጫ ማክበር ማለት ነው፡፡ የመቻቻል ባህል እንዳለ የሚያሳዩ አንዳንድ ማሳያዎች አሉ፡፡ ሰዎች በቋንቋ፣ በእሴት፣ በፖለቲካ፣ በሃይማኖት እና በአገራዊ ደረጃ እኩል ናቸው፡፡ የመቻቻል ባህል ያለዉ ማህበረሰብ ለቋንቋው፤ ለዘሩ፣ ለጎሳ እና ፆታ አድሎ የሌለው፤ ማኅበራዊ ግንኙነቱ በመከባበር፣ በሕዝባዊ ስምምነት፣ በትብብር እና በሰብአዊ ክብር ላይ የተመሠረተ ነዉ፡፡ ፖለቲካዊ ሂደቶቹ ገንቢ እና ዴሞክራሲያዊነት የተላበሱ፣ በቁጥር አነስተኛ የሆኑማህበረሰቦች ባሕላዊ አቋምና ቋንቋቸው ተጠብቆ የሚኖርበት፣ ሁሉም ሰው እኩል መብት የሚረጋገጥበት ነው፡፡

በተጨማሪም መቻቻልን የሚያመለክቱ አራት ዋና ዋና ክፍሎች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል:- እውቅና መስጠት፣ተቀባይነት፣ አክብሮት እና ማስተዋል ናቸው፡፡ ባህል ተሻጋሪ መስተጋብር ውስጥ ተቀባይነት እና እውቅና በዛሬው ጊዜ በሰዎች መካከል ያለውን ልዩነት ይበልጥ ለመረዳት ያግዛሉ፡፡

**የፅብረቃ ተግባር 5.2**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።**

1. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ የባህል መቻቻልን የሚያሳየዉ የቱ ነው?
   ሀ. ማጣጣል ሐ. ሌሎችን ማክበር
   ለ. የስዎችን ባህል ዝቅ ማድረግ መ. ለሌሎች ክበር አለመስጠት
2. ከሚከተሉት ውስጥ የመቻቻል ባህል የሌላቸው ሰዎች ባህሪ የትኛው ነው?
   ሀ. ጥላቻ ሐ. የፖለቲካ እኩልነትን ማክበር
   ለ. ሌሎችን ማክበር መ. የሃይማኖት ነጻነትን ማክበር
3. ከሚከተሉት ውስጥ ከሌሎች የሚለየው የትኛው ነው?
   ሀ. ኢ-ፍትሃዊነት ሐ. ሌሎችን መርዳት
   ለ. አንድን ሰው ከቡድን ማግላል መ. አካላዊ ጥቃት

## 5.3. የመቻቻል ባህል አስፈላጊነት

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- መቻቻል በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

መቻቻል ማለት የዓለማችንን ባህሎች፣ ሀሳቦች እና የሰው ልጅ የመሆን መንገዶቻችንን ማክበር እና ማድነቅ ነው። መቻቻል በልዩነት ውስጥ ስምምነት መፍጠር ነው። ይህም የሥነ-ምግባር ግዴታ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካና የሕግ መስፈርትም ነው። ሰላም እንዲሰፍን የሚያደርግ መልካም ባሕርይ የሆነው መቻቻል የጦርነት ባህል በሰላም ባህል እንዲተካ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ስለዚህ የመቻቻል ባህል የሚከተሉት ጥቅሞች አሉት።

- ✓ መቻቻል ተማሪዎች በቤተሰባቸው፣ በአካባቢያቸው እና በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ተስማሚ፣ የተረጋጋ፣ አስተማማኝ እና ዘላቂ ማህበራዊ ኑሮ እንዲኖራቸው ይረዳል፡፡
- ✓ መቻቻል በሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ሰላም እና ፍቅር እንዲሰፍን ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡
- ✓ መቻቻል ማለት በብዝሃነት ውስጥ ያለውን ጥንካሬ መገንዘብ ማለት ነው፡፡

ፅብረቃዊ ተግባር 5.3

- የመቻቻል ባህል አስፈላጊነት ምንድን ነው?

## 5.4 የመቻቻል ባህል ላይ ተጽእኖ የሚስከትሉ ምክንያቶች

የማነቃቂያ ጥያቄዎች

- የመቻቻል ባህል ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮች ምን ምን ናቸዉ?

‹‹የእያንዳንዳችሁ ፈታኝ ሁኔታ እነዚህን የመቻቻል እና የሌሎችን የመቻቻል እሳቤዎችን በመውሰድ በትምህርት ቤታችሁ፣ በማህበረሰባችሁ እና በሕይወታችሁ ላይ ተግባራዊ ማድረግ ነው››

- ➢ ከላይ በኔልሰን ማንዴላ የተጠቀሰው ጥቅስ መልእክት ምንድን ነው?

መቻቻል ለሌሎች የአኗኗር ዘይቤዎች፣ ማንነቶች፣ እሴቶች ወይም ልምዶች አዎንታዊ አመለካከትን ማሳየትን ያመለክታል፡፡ የተወሰኑ ልምዶች እና እሴቶች ወይም ደንቦች በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ይበረታታሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይሁን እንጂ የመቻቻል ባህል ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ አንዳንድ ምክንያቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ፡- እነዚህ የጭፍን ጥላቻ ልምድ መገለጫዎች፣ የበላይነት ስሜት፣ ያልተለመዱ አመለካከቶች፣ ጠበኛ ባህሪ፣ መለያየት፣ ወዘተ፡፡

**ፅብረቃዊ ተግባር 5.4**

1. የመቻቻል ባህል ላይ ተፅዕኖ ከሚያደርጉ ጉዳዮች ውስጥ ቢያንስ ሦስቱን ዘርዝሩ።

2. _____ ለሌሎች እሴቶች ወይም ልምዶች አዎንታዊ አመለካከት መያዝን ይጨምራል።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የመቻቻል ባህል ለሌሎች ሃሳቦች፣ አስተያየቶች እና ልምዶች ፍላጐት እና አሳቢነት የማሳየት መንገድ መሆኑን ተምራችኋል፡፡ የመቻቻል ባህል በሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ሰላምንና ፍቅርን በመፍጠር ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ የመቻቻል ባህልን የሚጐዱ ሌሎች አንዳንድ ምክንያቶችም አሉ፡፡ ለምሳሌ የመድልዎ ልምዶች፣ ጭፍን ጥላቻ፣ የበላይነት ስሜት፣ የተሳሳተ አመለካከት፣ ጠበኛ ባህሪ፣ መለያየት፣ ወዘተ፡፡

### ቁልፍ ቃላት

**የመቻቻል ባህል-** ማለት ለሌሎች ግለሰቦች አመለካከት፣ እምነትና ልማድ ፍትሃዊ፣ ዓላማ ያለውና ፈቃደኛ የሆነ አመለካከት መያዝ ማለት ነው፡፡

**መቻቻል** -ማለት በሰዎች ወይም በቡድን መካከል ሊኖሩ የሚችሉ ልዩነቶችን ሁሉ ማክበርና መቀበል ማለት ነው፡፡

## የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ

**ክፍል አንድ: አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. መቻቻል በሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ሰላምና ፍቅርን በመፍጠር ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታል።
2. የበላይነት ስሜት መቻቻልን ለማቆየት ሁነኛ መንገድ ነው።
3. የሌሎችን ባህላዊ ልምዶች ችላ ማለት ማህበራዊ አለመግባባት ሊያስከትል ይችላል።
4. የመቻቻል ባህል የሌላቸው ሰዎች ሁል ጊዜ የሌሎችን መብት ያከብራሉ።

**ክፍል ሁለት: ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።**

1. ከሚከተሉት ውስጥ ለመቻቻል አዎንታዊ አመላካች የሆነው የቱ ነው?

    ሀ. የቋንቋ እኩልነት አለመኖር ሐ. የማህበራዊ እኩልነት መኖር

    ለ. የሕግ እኩልነት አለመኖር መ. የፖለቲካ እኩልነት አለመኖር

2. ከሚከተሉት ውስጥ የመቻቻል ጥቅም የሆነው የትኛው ነው?

    ሀ. የማይስማማ ሕይወት እንዲኖር ይረዳል

    ለ. ሰላምን እና ፍቅርን በማቋቋም ረገድ ምንም ሚና የለውም

    ሐ. በማህበረሰቡ ውስጥ ግጭትን ያበረታታል

    መ. የአንድነትን መንፈስ ያበረታታል.

3. ከሚከተሉት ነገሮች መካከል የመቻቻል ባህልን ለማስፋፋት የሚረዳው የቱ ነው?

    ሀ. ያልተለመዱ አመለካከቶች ሐ. መለያየት

    ለ. እኩልነትን ማክበር መ. ጠበኛ ባህሪ

**ክፍል ሦስት፤ በአራት ወይም በአምስት ቡድኖች ተከፍላችሁ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ**

1. "የመቻቻል ባህል" ሲባል ምን ማለት ነው?
2. የመቻቻል ባህልን ማዳበር የምንችለው እንዴት ነው?

# ምዕራፍ ስድስት:

## የባህል ብዝሀነትን ማቻቻል

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፡-

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኂላ፡-

- በተለያዩ የህብረተሰብ አውድ ውስጥ የመቻቻል ፅንሰ-ሀሳብ ታብራራላችሁ፤
- በልዩነት አንድነት አስፈላጊነትን ታብራራላችሁ፤
- የባህል ልዩነቶችን ለማስተናገድ የመቻቻል አስፈላጊነትን ትገልጻላችሁ፤
- የባህል ልዩነቶችን ታብራራላችሁ፤
- የባህል ልዩነቶችን የማስተናገድ ባህልን ታሳያላችሁ፤

### መግቢያ

በምዕራፍ አምስት ውስጥ ስለ "መቻቻል" ባህል ጽንሰ-ሀሳብ በዝርዝር ተምራችኂል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ስለ ባህል ብዝሃነት መቻቻል ትማራላችሁ፡፡ እንዲሁም ምሳሌዎችን ትሰጣላችሁ፡፡ "የባህል ብዛሃነትን ማቻቻል" ማለት የእኛ ያልሆኑ ባህሎች ቢሆኑም እንኳን የማክበር አመለካከት ነው፡፡ ባህሎች የተዋሃደ፣ ሰላማዊ እና እርስ በእርሱ የሚስማማ ማህበረሰብ ለመፍጠር ይረዳሉ፡፡ እንደ ዜጋ የሌሎች ባህሎችን እንደራሳችሁ ባህል የማክበር እና የመቀበል ግዴታ አለባችሁ፡፡ ትምህርት ቤታችሁ የብዝሃነት ምርጥ ምሳሌ ነው፡፡ ብዝሀነታችሁ ትምህርት ቤታችሁን የበለጠ አስደሳች ቦታ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

## 6.1 የባህል ብዝሃነትን ማቻቻል

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

ለሚከተሉት ቃላቶች እና ሀረጎች ትርጉም ስጡ፡፡

- ብዝሃነት
- ብዝሃነትን ማቻቻል
- አድሎ
- የባህል ብዝሃነት ምንድን ነው?

የተለያዩ የአስተዳደር ዘይቤ እና ተሞክሮ ያላቸው ሰዎች በተወሰነ ቡድን ወይም ቦታ ላይ ሲሰበሰቡ የባህል ልዩነት ይከሰታል፡፡ በሃይማኖት፣ በቋንቋ እና በጎሳ ለሚኖር ብዝሃነት የራሳችን ተሞክሮ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይችላል፡፡ በማህበረሰባችሁ ውስጥ የሚታይ ብዝሃነት በትምህርት ቤታችሁ ውስጥም ሊታይ ይችላል፡፡

በተመሳሳይ እንዲህ አይነት ብዝሃነት በብሔራዊ ደረጃም ይታያል፡፡ ከሰማንያ በላይ ቋንቋዎች መነገራቸው፣ እንዲሁም የተለያዩ ሃይማኖቶች፣ ወጎች እና ልምዶች መገኘታቸው የኢትዮጵያን ብዝሃነት ያሳያል፡፡ ባህላዊ ብዝሃነት ያላት ሀገር የተለያዩ ቀለሞች እንደ ተሳሉ ስዕሎች ዉብና ማራኪ ናት፡፡ ስለሆነም የባህል ብዝሃነትን ማቻቻል ለተለያዩ ባህሎች፣ ልማዶች እና ልምምዶች አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖረን ይረዳናል፡፡



ስእል 6.1: የኢትዮጵያውያን ብዝሃነት

**ከዚህ በታች የቀረበዉን ስለ ብዝሃነት የተጻፈዉን ምንባብ አንብቡ እና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

ሁላችንም የተለያየን ነን ማናችንም አንድ ዓይነት አይደለንም፡፡ ልዩነት ወይም ብዝሃነት የሕይወት ቅመም ነው፡፡ ዛሬ ብዙ ማህበረሰቦች ብዝሃነት አላቸው፡፡ ሰዎች ከእነሱ የተለየ ባህል ካላቸው ሰዎች ጋር መስተጋብር ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ በሰዎች መካከል ያለው ይህ መስተጋብር ለሁሉም ሰው አዳዲስ ሀሳቦችን እና አመለካከቶችን ለመማር እድል ይሰጣል፡፡ የተለያዩ ባህሎች ካሏቸው ማህበረሰቦች የተለያዩ እምቅ ችሎታዎች እና ዕውቀቶች ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም የእያንዳንዱን ባህል ጥበባዊ ውበት እና ቅርስ መርሳት የለባችሁም፡፡ ሰዎች ከሌሎች ባህሎች ታሪኮችን፣ ዘፈኖችን እና ግጥሞችን መማር ይችላሉ፡፡

እነዚህ ሁሉ ልዩነቶቻችንን በማጥናት እኛ ኢትዮጵያውያን ልዩ የሚያደርገን ምን እንደሆነ መገንዘብ እንችላለን:: ስለ ሌሎች ባህሎች በመማር የራሳችንን ባህሎች ለሌሎች ማስተማርና እና ማጋራት እንችላለን:: አንዳንድ ሰዎች ብዝሃነትን የተግዳሮት ምንጭ አድረገው ያያሉ:: በእርግጠኝነት መናገር የሚቻለው ግን የተግዳሮቶች ምንጭ ብዝሃነት ሳይሆን ብዝሃነታችንን የምናስተናግድበት ሁኔታ ነው:: አንዳንድ ሰዎች ብዝሃነትን ያከብራሉ አንዳንዶች ደግሞ ይፈራሉ:: ይህንን ዓይነት አስተሳሰብ ደግሞ ለጭፍን ጥላቻ ይዳርገናል:: ሰዎችን በቋንቋዎቻቸው፣ በባህሎቻቸው ወይም በሌላ ማንነታቸው ላይ ተመስርቶ መጥላት ያለመሰልጠን ምልክት ነው:: ብዝሃነትን መሰረት ያደረጉ አለመግባባቶች ሲከሰቱ በተጠናከረ ጥረት በሰዎች መካከል ሊኖሩ የሚችሉ ብዝሃነትን አምኖ በመቀበል እና በማክበር ለጋራ ጥቅም በጋራ አብሮ መሥራት ይቻላል:: እኛ ሁላችንም የሰው ልጆች ነን እናም ብዙ ልዩነቶች ቢኖሩም ይህንን አለም አንድ ላይ መጋራት አለብን::

### ፅብረቃዊ ተግባራት 6.1

#### የውይይት ጥያቄዎች

1. ብዝሃነት በማህብረሰቡ ውስጥ ባይኖር ኑሮ ሕይወት ምን ሊመስል ይችላል?
2. ብዝሃነታችን በመማር ማስተማር ላይ ምን ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል?
3. ሰዎች ስለራሳቸዉ ብዝሃነት እንዲናገሩ ማበረታታት የእርስ በእርስ ግንኙነታቸውን ወደ ላቀ የጋራ መከባበር ይወስደዋል ብላችሁ ታምናላችሁ?

## 6.2 በብዝሃነት ውስጥ የአንድነት አስፈላጊነት



**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

- በልዩነት ውስጥ አንድነት ምንድን ነው?
- በልዩነት ውስጥ አንድነት ለምን ያስፈልጋል?
- ከላይ ከተጠቀሰው ሥዕል ምን ተመለከታችሁ?

"አንድነት ጥንካሬ ነው፤ ልዩነት ውበት ነው።" ስለዚህ በልዩነት ውስጥ አንድነት እና ጥንካሬ እንዲኖር በልዩነት ውስጥ ስምምነት፣ እኩልነት እና ሰላም አስፈላጊ ነው። በልዩነት አንድነት "ልዩነት ያለ አንድ ወጥነት" እና "ልዩነት ያለ መበታተን" ጽንሰ-ሀሳብ ውጤት ነው። ብዝሃነትና አንድነት ሰዎች ግንኙነታቸውን የሚያበለጽጉበት በመሆን ላይ የተመሠረተ ነው። ይህ ዓይነቱ ጥንካሬ አገሪቱን ከጠላቶች ለመጠበቅ እና ድህነትን በመዋጋት እየታገሉ ለመኖር እና በሰላም አብሮ የመሥራት እድልን ከፍ ለማድረግ ይረዳል። በልዩነት አንድነት በሥራ ቦታ፣ በትምህርት ቤቶች እና በማህበረሰቦች ውስጥ የሰዎችን ሥነ-ምግባር ይጨምራል። በልዩነት አንድነት አፈፃፀምን፤ የሥራ ጥራትን፤ ምርታማነትን እና የአኗኗር ዘይቤን በማሻሻል በሰዎች መካከል የተሻለ ቅንጅት፣ ግንኙነት እና የቡድን ስራን ያበረታታል።

በኢትዮጵያ ውስጥ የሕብረተሰቡ አባላት አንዳቸው ከሌላው ጥቅም እንዲያገኙ የሚረዱ ባህላዊ ማህበራት አሉ። እነሱም እድር፤ ደቦ እና ማህበርን ያካትታል። የእነዚህ ማህበራት ግቦች ሰዎች አንድ ላይ ተሰባስበው በተናጥል ሊከናወኑ የማይችሉ ተግባራትን ለማከናወን እንዲተባበሩ መርዳት ነው። እድር በእድሩ አባላት የጋራ ስምምነት የተቋቋመ ባህላዊ ተቋም ነው። ስለሆነም አባሎቻቸው ወይም የቤተሰባቸው አባላት አደጋ ሲያጋጥሟቸው አባላቱ አንዳቸው ከሌላው ድጋፍ እንዲያገኙ ይረዳል። የእድር ዋና ተግባር የቤተሰብ አባላት ሲሞቱ የቀብር እና የማጽናናት ተግባራትን ማስተናገድ ነው። እድር በአካባቢው የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ትልቅ ሚና ይጫወታል። እድር የህብረተሰቡን ኑሮ ለማሳደግ በሚችሉ የተለያዩ ዓላማዎችን ለማሳካት የአባላቱን ነፃ ጉልበት ያስተባብራል። ደቦ ከእድር ጋር ተመሳሳይ ነው። ደቦ ከእድር የሚለየው አባላትን በእርሻ እና ሌሎች እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲደጋገፉ አላማ ማድረጉ ነው።

የግለሰቦችን መንፈሳዊ ተግባር ለመፈፀም ማህበር ሊቋቋም ይችላል። አብዛኛዎቹ ጉዳዮች የማህበር አባላት በተመሳሳይ ጉባኤ ውስጥ የሚያመልኩ ሰዎች፣ የቅርብ ጓደኞች፣ ጎረቤቶች እና ዘመዶች ናቸው። የማህበሩ አባላት ተራዎችን በመውሰድ በየወሩ ትንንሽ ድግሶችን የማዘጋጀት ግዴታ አለባቸው። የማህበር አባላት በችግር ጊዜ እርስ በእርስ ይደጋገፋሉ። ከአባላቱ ውስጥ አንዱ ከታመመ ይጠይቃሉ። የታማሚዉን ወጪዎች ለመሸፈን ገንዘብ ያዋጣሉ። አንዳቸው የሌላውን ቤተሰቦች የጋብቻ ሥነ ሥርዓት በተመለከተም ይረዳዳሉ።



ስዕል 6.2: ሰዎች በጋራ ሲሰሩ (ደቦ)

## ፅብረቃዊ ተግባር 6.2

1. በአካባቢያችሁ ስለሚተገበሩ እድር፣ ማህበር እና ደቦ ጥቅሞች ተወያዩ::
2. የሚከተለውን ተረት አንባቡ እና ተከታይ ጥያቄዎችን መልሱ::

## ስለ አንድነት ሃያልነት ተረት

አንድ ጊዜ አንድ አዛውንት በጣም ታመው በአልጋቸው ላይ ይተኛሉ:: አዛውንቱ እርስ በእርስ የሚጋጩ አራት ወንዶች ልጆች ነበሯቸው:: እሳቸው ሁል ጊዜ ስለ እነሱ ይጨነቁ ስለ ነበር ትምህርት ሊያስተምሯቸው ፈለጉ እና ልጆቻቸውን ወደ እርሳቸው እንዲመጡ ጠየቋቸው:: ልጆቹ ወደ እርሳቸው እንደመጡም አዛውንቱ አባታቸው ለልጆቻቸው በአንድ ላይ የታሰሩ ዱላዎችን ሰጧቸው እና እንዲህ ሲሉ ጠየቋቸው "እነዚህን ዱላዎች መስበር ትችላላችሁ?" ለአባታቸው ጥያቄ የልጆቹ ምላሽ አዎንታዊ ነበር:: ከዚያም:-

የመጀመሪያው ልጅ በአንድ ላይ የታሰረውን ዱላ ለመስበር ሞከረ አልቻለም ኃይሉን አሰባስቦም እንደገና ሞከረ ግን አልቻለም እና ተሰፋ ቆረጠ፡፡ከዚያ ዕድሉን ለመሞከር የሁለተኛው ልጅ ተራ ሆነ፡፡ ልጁ የአባታቸው ትእዘዝ ቀላል ሥራ እንደሆነ ያስብ ስለ ነበር በቀላሉ ዱላዎችን ለመስበር ሞከረ ግን ምንም አልቻለም፡፡ ከዚያ እድሉ የሦስተኛው ልጅ ሆነ እሱም ልክ እንደ ወንድሞቹ ዱላዎችን ለመስበር ጥረት አደረገ ግን ምንም አልቻለም፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ታናሹ ወንድ ልጃቸው እራሱን ብልህ እና ዱላዎችን በአንድ ግዜ መስበር የሚችል፤ ወንድሞቹን ግን ብቃት እንደሌላቸው አድርጎ ይቆጥር ስለነበር ጮኸባቸው፡፡ ከዚያም እሱ ሁሉንም ዱላዎች አንድ በአንድ መስበር ቻለ፡፡

ከዚያ በኋላ አዛውንቱ አባታቸው በልጆቻቸዉ ላይ ፈገግ አሉና ቀጣዩን ጥያቄ እና ምክር አካፈሏቸው፡፡አዛውንቱ "ልጆቼ ምን እንደ ሆነ ተረድታችኋል? ዱላዎቹን አንድ በአንድ መስበር ቀላል ነው አብረው ወይም በአንድ ላይ ሲሆኑ ግን ማንም ሊሰብራቸው አይችልም፡፡ ስለዚህ እናንተ አራት ወንድማማቾችም ሁል ጊዜ አንድ ላይ መሆን ብትችሉ ማንም እናንተን ሊጎዳችሁ ወይም ሊያጠቃችሁ አይችልም፡፡" ሲሉ መከሯቸው፡፡ ከዚያን ቀን ጀምሮ አራቱ ወንድማማቾች የአባታቸውን ምክር እና ትምህርት በመስማት ጠላትነታቸውን ረሰተው በአንድ ላይ በመሆን ጥንካሬያቸውን አግኝተው በሰላም መኖር ቻሉ፡፡

- ከላይ ከተጠቀሰው ተረክ ምን ተረዳችሁ?

በአጠቃላይ

- አንድነት በብዝሃነት፡- ሰዎች በትምህርት ቤት፣ በሥራ ቦታ እና በማህበረሰብ ውስጥ ያላቸውን ሥነ ምግባር ይጨምራል፡፡

- በግለሰቦች መካከል የሚኖርን ግንኙነት እና ትብብርን ለማሻሻል ይረዳል፡፡ በዚህ መሠረት ውጤታማነትን፣ የሥራ ጥራትን፣ ምርታማነትን እና የአኗኗር ዘይቤን ያሻሽላል፡፡
- በመጥፎ ሁኔታ ውስጥ እንኳን ግንኙነትን ውጤታማ ያደርጋል፡፡
- አለመግባባቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመፍታት ይረዳል፡፡
- ጤናማ የሆነ ግንኙነትን ያሻሽላል፤ እንዲሁም ለሁሉም በእኩልነት ሰብዓዊ መብቶችን ይጠብቃል፡፡
- አንድነት በብዝሃነት፡- በዜጎች መካከል የብሔራዊ ውህደት ልማድን ያመጣል፡፡
- አንድነት በብዝሃነት፡- ሀገራችንን ያሻሽላል፤ እንዲሁም ያበለፅጋል፡፡

**ዕብረቃዊ ተግባር 6.3**

በሚከተሉት ነጥቦች ዙሪያ ተወያዩ እና በመማሪያ ደብተራችሁ ላይ መልሳችሁን ፃፉ፡፡

1. የጓደኞቻችሁን የተለያዩ ማንነቶች ማክበር ጥቅሞች ምንድን ናቸው?
2. በልዩነት ውስጥ አንድነትን ሳናስተካክል ስኬታማ ትምህርትን ማሳደግ እንችላለን?
3. አንድነት በብዝሃነት ያለውን ሁለት ጥቅሞችን ፃፉ፡፡

## 6.3 በባህል ብዝሃነት ውስጥ የመቻቻል አስፈላጊነት

መቻቻል አንድን ሰው፣ ቡድን ወይም ማህበረሰብ በእነሱ ዋጋ፣ በጎነት፣ ክብር እና መከባበር ላይ ተመሥርተን መቀበል ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም የሌሎችን እምነት፣ የአኗኗር ዘይቤዎችን እና አመለካከቶችን ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን መቻል ነው፡፡

እንደ ዜጋ የሌሎችን ባህል እንደራሳችሁ ጥሩ ባህል መሆኑን መቀበል አለባችሁ:: ሌሎች የሚይዙትን አመለካከቶች ለማዳመጥ ፈቃደኛ መሆን ይጠበቅባችኋል:: የተለያዩ ሃይማኖቶች፣ ቋንቋዎች እና ባህሎች ካላቸዉ ሰዎች ጋር መኖር ይጠበቅብናል፡፡ ሌሎች ከእናንተ የተለዩ ከሆኑ እና የበለጠ ለመማር ፈቃደኛ ከሆናችሁ መቻቻልን ታዳብራላችሁ፡፡ እነሱን መረዳት ስትችሉ እነሱም ይረዷችኋል፡፡ መቻቻል በሰላም አብሮ ለመኖር ቁልፍ ነገር ነው::

### ዉስን ጥናት 1፡ የትምህርት ቤት ጓደኞማኞች

አዚዛ፣ ቶሎሳ፣ ይርጋ፣ መብራት እና ልዑል የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሲሆኑ አምስቱም የቅርብ ጓደኞች ናቸው:: አዚዛ ሙስሊም፤ ቶሎሳ ፕሮቴስታንት፤ ይርጋ የይሖዋ ምስክር ሃይማኖት ተከታይ ሲሆኑ መብራት እና ልዑል ደግሞ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው፡፡ እነዚህ ጓደኞሞች የተለያዩ ጎሳዎች አባል ሲሆኑ ይርጋ ጉራጌ፣ አዚዛ ሀረሪ፣ ቶሎሳ ኦሮሞ፣መብራት አማራ፣ ልዑል ደግሞ ትግሬ ናቸው:: እነሱ በራሳቸው ሃይማኖት፣ ቋንቋ እና በሌሎች ባህሎቻቸዉ በጣም ኩራት ይሰማቸዋል:: እንደ ጓደኛ ባህሎቻቸዉን ይጋራሉ:: በተመሳሳይ እይታ አንዳቸው የሌላኛውን ባህል ያከብራሉ:: የትምህርት ዓመቱ ሲያልቅ ወደ አንኮበር ለመሄድ እና ከመብራት ዘመዶች ጋር ለሁለት ቀናት እዚያ ለመቆየት ተስማምተዋል:: በሚቀጥለው ዓመት የትምህርት አጋማሽ ዕረፍት ወቅት ደግሞ ቶሎሳ እነሱን ወደ ሰበታ በመዉሰድ የዘመዶቹን የአኗኗር ዘይቤ ለማስጎብኘት ቃል ገብቷል፡፡



ምስል 6.4 ከተለያዩ አካባቢዎች የመጡ ተማሪዎች በአንድ ላይ

የጽብራቃ ተግባር 6.4

1. ከላይ የተቀመጠዉ ዉስን ጥናት የባህል ብዝሃነት መቻቻልን የሚያሳይ ይመስላችኋል?
2. ከተረኩ ምን ተማራችሁ?

## 6.4. የባህል ብዝሃነትን መቀበል

የማነቃቂያ ጥያቄዎች

- በክፍላችሁ ውስጥ ስላለው የባህል ብዝሃነት ምን ይሰማችኋል?
- ብዝሃነትን የማቻቻል ሀላፊነት ያለበት እና ተጠቃሚው ማን ነው?

የኢትዮጵያ ህዝቦች የተለያዩ ማንነቶች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶች፣ ባህሎች፣ የፖለቲካ አመለካከቶች እና ሌሎች ብዙ መስተጋብሮች ውጤት ናቸው። ማንም ሰው ሙሉ በሙሉ እራሱን እንዲህ ብቻ ነኝ ብሎ መግለፅ አይችልም።

እኛ የምንኖረው ብዝሃነት በበዛበት ዓለም ውስጥ ነው፡፡ የባህል ብዝሃነትን መረዳት ማለት የእኛ ያልሆኑትን ባህሎች የኛን ባህሎች በምንረዳበት መንገዶች እንገነዘባለን እንዲሁም እናከብራለን ማለት ነው፡፡ ከሌሎች የባህል ባለቤቶች ጋር የታማኝነት፣ የመቻቻል እና የመረዳዳት ድልድይን መገንባት እንችላለን፡፡ በተጨማሪም ብዝሃነታችን ትምህርት ቤታችንን ይበልጥ አስደሳች የመማሪያ ቦታ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ከተለያዩ ባህሎች የመጡ ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታን፣ አዳዲስ መንገዶችን፣ አዳዲስ እውቀቶችን፣ አስተሳሰቦችን እና የተለያዩ ልምዶችን ያበረክታሉ፡፡ ከብዝሃነታችን እርስ በእርሳችን መማማር እንችላለን፡፡

ስለ ትብብር እና አብሮ መስራት ለማሰብ መጀመሪያ አንዳችን የአንዳችንን ማንነት እና ባህል የመረዳት ፍቃደኝነት ሊኖረን ይገባል፡፡ የሌሎችን ባህሎች መረዳት እኛ በምንማርበት ትምህርት ቤት ውስጥ የተለያዩ አመለካከቶችን እንድንረዳ ይረዳናል፡፡ የተለያዩ አሉታዊ አመለካከቶችን እና አድልዎችን ለማስወገድ ይጠቅመናል፡፡ የሌሎችን ባህሎች ማጥላላት ግን ወደ ግጭት ሊወስደን ይችላል፡፡ ስለሆነም ብዝሃነትን በማክበርና ባህሎችን በእኩልነት በማየት አብረን እንስራ፤ ድህነትንም እንዋጋ፡፡




ስዕል 6.5 የኢትዮጵያ የብዙሃንነትን ባህል ምሳሌዎች

**የፅብረቃ ተግባር 6.5**

በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ተወያዩ፡፡

1. የብዝሃነት ጥቅም ምንድን ነው?
2. የባህላዊ ብዝሃነትን ማቻቻል ለማህበራዊ ደህንነታችን እንዴት አስተዋፅኦ ያደርጋል?

**ውስን ጥናት፡ ባህላዊ ጭፈራ**

አቶ አገኘሁ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ4ኛ ክፍል የሞራል ትምህርት መምህር ነው፡፡ የባህል ብዝሃነት እና የመቻቻል ትምህርትን አስተምሮ ከጨረሰ በኋላ ለተማሪዎቹ ተጨማሪ ተግባራት ሰጠ፡፡ ተጨማሪ ተግባራቱም የተማሪዎች ወላጆች የራሳቸዉን የባህላዊ ጨዋታዎች እንዲያሠለጥኗቸው ይጠይቃል፡፡ ተማሪዎች ሰኞ ወደ ትምህርት ቤት ሲመጡ ሁሉም ከወላጆቻቸው በቤት ውስጥ የተማሯቸውን ጭፈራዎች እና ሙዚቃዎች ለማሳየት ዝግጅት አድርገው ነበር፡፡ ሙዚቃዎቹን እና ጭፈራዎቹን በመድረክ ላይ ሲያከናውኑም መላው የክፍል ተማሪዎች ተሳትፎ ያደርጉ ነበር፡፡ በዝግጅቱ ላይ የተለያዩ ባህላዊ ሙዚቃ እና ጭፈራዎች በተማሪዎች ተከናውነዋል፡፡ የማይረሳ ተሞክሮ ነበር፡፡ ሁሉም ሰው የሚያስታውሰው አጋጣሚም ነበር፡፡ እያንዳንዱ ተማሪ ስለ ተናገሯቸው የተለያዩ ቋንቋዎች እና ስለ ኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃ እና ጭፈራዎች ያገኙት እውነተኛ የመማሪያ ዕድል ሆኖም ነበር፡፡

**ውይይት**

- ቡድን በመመስረት ከተለያዩ ባህላዊ ጭፈራዎች ምን መማር እንደምትችሉ ተወያዩ፡፡ የቡድን መሪዎች ሀሳቦችን ለተቀረው የክፍል ተማሪዎች ያቅርቡ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ መቻቻል እና ብዝሃነት ጽንሰ-ሀሳቦች ተምራችኋል። የባህል ብዝሃነትን ለመቀበል እና ለማክበር፣ በብዝሃነት ውስጥ የአንድነትን አስፈላጊነት፣ የብዝሃነት አና መቻቻል አስፈላጊነት በኢትዮጵያ እና ከትምህርት ቤታችን አውድ እንዴት ማስተናገድ እንደሚቻል ተምራችኋል። ትምህርቱ የአኗኗር ዘይቤያችንን ለማበልፀግ ይረዳናል። እያንዳንዱ ባህል ለአገራችን ልማት አስተዋፅኦ ስለ ሚያበረክት የባህል ብዝሃነትን ማክበር ጥቅሞች አሉት። ባህላዊ ልዩነቶችን ስናከብር እና በእኩልነት ስናይ ከባህላችን ተጠቃሚ መሆን እንችላለን። የሌሎችን ባህሎች ማጥላላት በተለያዩ ባህላዊ ቡድኖች መካከል ግጭቶችን ሊፈጥር ይችላል። ስለሆነም ብዝሃነትን ማክበር እና ባህሎችን በእኩልነት ማየት ያስፈልጋል። ይህ አንድ ላይ እንድንሠራ እና ድህነትን እንድንዋጋ ይረዳናል። ድህነት የጋራ ጠላታችን ነው።

### የቃላት መፍቻ

**ብዝሃነት:** በሰዎች ሕይወት የአኗኗር ዘይቤ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖቶች፣ በባህሎች፣ በፖለቲካ አስተሳሰብ እና በመሳሰሉት የተለያዩ መሆናቸውን ይገልጻል።

**ብዝሃነትን ማቻቻል-** ማለት ሰዎች የጎሳ፣ የሃይማኖት፣ የቋንቋ፣ ወይም ሌሎች ልዩነቶች ቢኖሯውም በመከባበር አብረው መኖራቸውን ያመለክታል።

## የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ

**ክፍል አንድ፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ "እዉነት" ትክክል ካልሆነ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ።**

1. የባህል ብዝሃነት ለአገራችን እድገት አስተዋፅኦ ያደርጋል።
2. የባህል ብዝሃነትን ስናከብር ከባህላችን ተጠቃሚ እንሆናለን።
3. የሌሎችን ባህሎች ማጥላላት ለተለያዩ ባህላዊ ቡድኖች ወደ ግጭት መግባት ምክንያት ሊሆን ይችላል።
4. ልዩነቶችን ማክበር እና ባህሎችን በእኩልነት ማየት የለብንም።

**ክፍል ሁለት፡ እራስን የመገምገም መልመጃ**

| | የባህሪ አመላካች | እስማማለሁ | አልስማማም |
|---|---|---|---|
| 1 | በሁሉም ሰዎች ውስጥ ጥሩነትን ማግኘት እችላለሁ። | | |
| 2 | በቤተሰቤ እና በሀገሬ ቅርሶች እኮራለሁ። | | |
| 3 | በቤተሰቤ እና በትምህርት ቤቴ ውስጥ የሰላም ጠባቂ እሆናለሁ። | | |
| 4 | በሌሎች ሰዎች ላይ የሚያፌዙ ቀልዶችን አልናገርም ወይም አልሰማም። | | |
| 5 | ሁሉም ልጆች በራሳቸው መንገድ የተለያዩ እና ልዩ ሊሆኑ እንደሚችሉ አምናለሁ። | | |
| 6 | ሁሉም ልጆች መወደድ እና መከበር ይገባቸዋል ብዬ አምናለሁ። | | |
| 7 | በሁሉም ልጆች ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረኝ እና ጥሩ ጓደኛ ለመሆን እሰራለሁ። | | |
| 8 | በትምህርት ቤቴ ውስጥ ስለ ሌሎች ልጆች የቤተሰብ ወጎች የቻልኩትን ያህል እማራለሁ። | | |

**ክፍል ሦስት፡ በሚከተሉትን ጥያቄዎች ዙሪያ ተወያዩ።**

1. ለምን ለብዝሀነት እና ለእኩልነት ትኩረት እንድንሰጥ የተፈለገዉ ለምን ይመስላችኋል?
2. ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች የመጡ ሰዎችን ማክበር ጥቅሞች ምንድን ናቸው?
3. አድልዎን ለመቀነስ ምን እርምጃዎችን መውሰድ እንችላለን?

**ክፍል አራት፡ ከዚህ በታች ለተሰጡ ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ዉስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።**

1. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የባህል ብዝሃነት ጥቅም አይደለም?

   ሀ. እያንዳንዱ ባህል ለህብረተሰቡ አንዳንድ እሴቶችን ያበረክታል።

   ለ. አለመግባባቶች ግጭት እና ጦርነት ያስከትላሉ።

   ሐ. የተለያዩ የአለባበስ ዘይቤዎች እና ጭፈራዎች መኖራቸው ደስ የሚል ነው።

   መ. የተለያዩ ባህሎች መኖራቸው የቱሪስቶችን ትኩረት ይስባሉ።

2. ከሚከተሉት አንዱ የብዝሃነት አንድነት ጥቅም አይደለም?

   ሀ. ትብብርን ማሻሻል

   ለ. የሰዎችን ግብረ-ገብነት መጨመር

   ሐ. የሥራ ጥራትን እና ምርታማነትን መቀነስ።

   መ. ተግባቦትን ውጤታማ ማድረግ።

3. ከተለያዩ ባህሎች የሚመጡ ተማሪዎች ከአንዱ በስተቀር የሚከተሉትን አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ።

   ሀ. የቋንቋ ችሎታዎችን          ሐ. አዳዲስ የአስተሳሰብ መንገዶችን

   ለ. አዳዲስ እውቀትን          መ.ተመሳሳይ ልምዶች

4. አባላቱ በየወሩ በየተራ አነስተኛ ዝግጅት የማዘጋጀት ግዴታ ያለባቸው በየትኛው ባህላዊ ማህበር ነው?

   ሀ. እቁብ          ለ. ደቦ          ሐ. እድር          መ.ማህበር